# የሴቶችን ተፈጥሯዊ ደም የተመለከተ አጭር መልዕክት

ጸሐፊ የተከበሩ ሸይኽ
*ሙሐመድ ቢን ሷሊሕ አል'ዑሠይሚን*
እርሳቸውን፣ ወላጆቻቸውንና መላው ሙስሊሞችን መሀርታውን ይለግስ

*

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው።

ምስጋና ሁሉ ለአላህ የተገባ ነው፤ እናመሰግነዋለን፤ እርዳታውንም እንለምነዋለን፤ ምህረቱንም እንማፀነዋለን፤ ወደ እርሱም በንሰሀ እንመለሳለን፤ ከነፍሶቻችን ክፋትና ከመጥፎ ሥራዎቻችንም በአላህ እንጠበቃለን። አላህ የመራውን የሚያጠመው የለም፤ ያጠመመውንም የሚመራው የለም፤ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የሌለ ብቸኛና ተጋሪ የሌለው መሆኑን እመስክራለሁ፤ ሙሐመድም የአላህ ባሪያና መልዕክተኛው መሆናቸውንም እመሰክራለሁ፤ የአላህ ሰለዋትና ሰላም በእርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው እንዲሁም እስከ ቂያማ ቀን ድረስ በመልካም በተከተሏቸው ላይ ይስፈን። በመቀጠልም፦ ሴትን የሚያጋጥማት የደም ዓይነቶች ማለትም የወር አበባ ደም፣ የኢስቲሓዷህ ደም እና የድህረ ወሊድ ደም ሊብራሩ ከሚገባቸው፣ ብይናቸውንም በሚገባ ሊረዷቸውና በጉዳዩ የተነገሩት ትክክልና ስህተቱን ሊለዩ ከሚገባቸው ጉዳዮች መካከል ነው። የእነዚህ ጉዳዮች አመዛኙን እና ደካማውን አቋም ለመለየት ደግሞ ከቁርኣንና ከሱና በተገኙ ማስረጃዎች ላይ መመርኮዙ የግድ ነው።

1- ምክንያቱም አላህ በባሮቹ ላይ እርሱን እንዲያመልኩበት የደነገገውና ኃላፊነትም የሰጠባቸውን ህግጋቶች የተመሰረቱባቸው ሁለት መሰረታዊ ምንጮች በመሆናቸው ነው።

2- እንዲሁም በቁርኣን እና ሱንና መመርኮዝ ለቀልብ እርጋታ፣ ለልብ መከፈት፣ ለነፍስ እርካታ ኃላፊነትን ከጫንቃ ለማውረድ የሚረዳ ዓይነተኛ መፍትሄ በመሆኑ ነው።

3- ምክንያቱም ከሁለቱ ውጭ ላለው ማስረጃ ይፈለግለታል እንጂ ማስረጃ አይሆንም።

በአላህና በመልዕክተኛው ሶለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ቃል ካልሆነ በቀር ማስረጃ የለምና። ከዚህ በተጨማሪ አመዛኝ በሆነው የዑለሞች እይታ መሰረት ቁርኣንና ሓዲሥን የሚቃረን እስካልሆነ ድረስ ከሶሓቦች መካከል የሆኑ ዑለሞች ቃልም እንዲሁ ማስረጃ ነው። እንዲሁም እንደተጨማሪ ቅድመ መስፈርት የሌላን ሰሓባ ንግግርንም የማይቃረን ከሆነ ነው። በዚህ መሰረት ቁርኣን እና ሱና ውስጥ ንግግሩን የሚፃረር ነገር ካለ ቁርኣን እና ሱና ውስጥ ያለውን መያዝ ግዴታ ነው። የአንድ ሰሓብይ ንግግር የተፃረረው ከሌላኛው ሰሓብይ ንግግር ጋ ከሆነ ከሁለቱ ንግግሮች መካከል በማስረጃ ሚዛን የሚደፋውን አቋም አጣርቶ ይበልጥ ለእውነት የቀረበውን አቋም መያዝ ይገባል። ምክንያቱም የበላይ የሆነው አላህ እንዲህ ብሏልና፦ {እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገዙ። መልክተኛውንና ከእናንተም የስልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ። በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትሆኑ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና ወደ መልክተኛው መልሱት። ይህ የተሻለ መጨረሻውም ያማረ ነው።} [አን'ኒሳእ፡ 59]

ይህ እነኝህን የደም ዓይነቶችንና ያላቸውን ፍርድ (ብይን) የሚዳስስ አጭር መልዕክት ነው። የሚከተሉትን ክፍሎችንም አካትቷል፦

ምዕራፍ አንድ፡ የወር አበባ ምንነት እና ሚስጢሩን በተመለከተ
ምዕራፍ ሁለት: የወር አበባ መጀመሪያና መጨረሻ ጊዜ
ምዕራፍ ሦስት: በወር አበባ ወቅት የሚያጋጥም መለዋወጥ
ምዕራፍ አራት፡ የወር አበባን የተመለከቱ ሕግጋት
ምዕራፍ አምስት፡ የኢስቲሓዷ ደም እና ሕግጋቱ
ምዕራፍ ስድስት፦ ስለ ወሊድ ደም እና ሕግጋቱ
ምዕራፍ ሰባት፦ የወር አበባን የሚከለክል ወይም የሚያመጣን ነገር ስለ መጠቀም እንዲሁም እርግዝናን ስለመከላከል እና ስለ ማስወረድ

*

## ምዕራፍ አንድ፡ የወር አበባ ምንነት እና ሚስጥሩን በተመለከተ

ሐይድ ማለት ቋንቋዊ ትርጓሜው፦ የአንድን ነገር መፍሰስ ወይም መጓዝ የሚያመለክት ቃል ነው።

ሸሪዓዊ (ቴክኒካዊ) ትርጓሜው ደግሞ፦ በተፈጥሮ ያለምንም እክል በሴት ላይ ለታወቁ ጊዜያት የሚከሰት ደም ነው። በህመም፣ በቁስል፣ በማስወረድ ወይም በመውለድ መንስኤነት ሳይሆን በተፈጥሯዊ ዑደት ሳቢያ የሚፈስ ደም ነው። ተፈጥሯዊ (መደበኛ) ደም እንደመሆኑ መጠን እንደ ሴቷ፣ እንደ አካባቢዋ እና እንደ አየሩ ሁኔታ ይለያያል። ከዚህም አንፃር ሴቶች ጉልህ በሆነ መልኩ ይለያያሉ።

በውስጡ ያለው ጥበቡም፦ ሽሉ በእናቱ ማኅፀን ውስጥ ሳለ ከማህፀን ውጭ የሆነ ሰው በሚመገበው መልኩ ሊመገብ ስለማይችል ለእርሱ እጅግ በጣም የሚያዝንለት አካል ቀለቡን ሊሰጠው አይችልም። ስለዚህም የበላይ የሆነው አምላክ በእናቱ ማኅፀን ውስጥ ሳለ ሽሉ መመገብና መፍጨት ሳይጠበቅበት ፅንሱ ቀለቡን የሚያገኝበትን የደም ስርአት ዘረጋለት። ቀለቡ በእምብርቱ በኩል ወደ ደም ሥር ውስጥ ገብቶለት ከእሱ እንዲመገብ ሆነ። ውብ አድርጎ ፈጣሪው አላህ ላቀ።

ይህ ነው እንግዲህ በወር አበባ ውስጥ ያለው ጥበብ፤ ለዚያም ነው አንዲት ሴት ካረገዘች በኋ የወር አበባዋ የሚቋረጠው፤ ቢመጣ እንኳ እምብዛም የሆነው። ልክ እንደዚሁ ጡት የሚያጠቡ ሴቶች በተለይም በመጀመሪያዎቹ ጡት የማጥቢያ ጊዜያት ላይ ያሉ ሴቶችም የወር አበባቸው ይቀንሳል።

*

## ምዕራፍ ሁለት: የወር አበባ የሚጀምርበት እና የሚያቆምበትን የጊዜ ገደብ በተመለከተ

ይህንን ምዕራፍ ከሁለት አቅጣጫ በኩል እንዳስሰው፡-
የመጀመሪያው፦ የወር አበባ የሚጀምርበት ዕድሜ
ሁለተኛው፦ የወር አበባ የሚዘልቅበት የጊዜ ቆይታ
የመጀመሪያው ጉዳይ፦ የወር አበባ በብዛት የሚከሰትበት የዕድሜ ክልል ከአስራ ሁለት አመት እስከ ሃምሳ ዓመት መካከል ባለው ነው። ምናልባትም ሴቷ እንደ ሁኔታዋ፣ እንደ አካባቢዋ እና እንደ አየሩ ሁኔታ የወር አበባዋ ከጠቀስነው ጊዜ ቀድሞ ሊጀምርም ዘግይቶ ሊዘልቅም ይችላል።
የኢስላም ሊቃውንት አላህ ይዘንላቸውና አንዲት ሴት የወር አበባ ማየት የምትጀምርበትና የምታቆምበት የተወሰነ ገደብ አለው ወይ? ከእርሱ በፊትም ሆነ በኋላ የወር አበባ ታያለች ወይስ አታይም? ከተወሰነው ጊዜ በፊትም ሆነ በኋላ የምታየው ደምስ የወር አበባ ሳይሆን የተበላሸ ደም ነው? በሚለው ጉዳይ ላይ በመካከላቸው የሀሳብ ልዩነት አላቸው።
በዚህ ርዕስ ላይ የኢስላም ምሁራን በሀሳብ ተለያይተዋል፤ ዳሪሚይ እነዚህን የሀሳብ ልዩነቶች ከጠቀሱ በኋላ እንዲህ ብለዋል፦ እነዚህ ሀሳቦች ሁሉ በእኔ እይታ ስህተት ናቸው! ምክንያቱም የዚያ ሁሉ ማመሳከሪያው ተጫባጩ ነውና። በመሆኑም ይብዛም ይነስም በማንኛውም ሁኔታ እና ዕድሜ የተከሰተ የወር አበባ መሆን አለበት። አላህ ይበልጡኑ ያውቃል።
እውነታውም ይህ አድ'ዳረሚ የተናገሩት ሀሳብ ነው። የሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ ምርጫም ይህው ነው። ስለዚህ አንዲት ሴት በየትኛውም (ዕድሜዋ) የወር አበባ ካየች ዕድሜዋ ከዘጠኝ ዓመት በታችም ሆነ ከሀምሳ በላይ ከሆነ ቢሆን የወር አበባዋ ነው (ተብሎ ይታሰባል)። ምክንያቱም አላህና መልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) የወር አበባን ብይን ያቆራኙት ከተጨባጩ ጋር ነውና። አላህና መልዕክተኛውም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) በተወሰነ የዕድሜ ክልል ብቻ ገድበው አልገለጹትም። በመሆኑም ብይኑ ወደ ተቆራኘበት ተጨባጭ መመለሱ የግድ አስፈላጊ ሆነ፤ በተወሰነ የዕድሜ ክልል ለመገደብም የቁርኣን ወይም የሱና ማስረጃ ያስፈልጋል፤ ለዚህ የሚሆን ማስረጃ ደግሞ የለም።
ሁለተኛው ርዕስ ደግሞ፤ የወር አበባ የሚዘልቅበትን ጊዜ የተመለከተ ነው። ማለትም የሚቆይበትን የጊዜ መጠን ነው።
በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የኢስላም ሊቃውንት እስከ ስድስትና እስከ ሰባት ዓይነት የደረሰ በርከት ያለ የአቋም ልዩነት አሳይተዋል፤ ኢብኑል ሙንዚር (አላህ ይዘንላቸው) እንዲህ ብለዋል፦ የተወሰኑት እንዲህ ብለዋል፦ የወር አበባ ደም የሚታይበት ዝቅተኛም ሆነ ከፍተኛ የብዛት ገደብ የለውም።
እኔም እንዲህ አልኩ፦ ይህ አባባል (አቋም) ቀደም ሲል እንደጠቀስነው የአድ'ዳሪሚ ንግግር (አቋም) ነው። የሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ ምርጫም ይህው ነው። አመዛኙም (ትክክለኛው) አቋም ይህ ነው። ምክንያቱም ቁርኣን፣ ሱና እና አስተውሎት (ወደዚህ) ስለሚያመላክቱ ነው።
የመጀመሪያው ማስረጃ፦ የበላይ የሆነው አላህ ተከታዩ ቃሉ ነው፦ "ከስለ ወር አበባም ይጠይቁሃል። እርሱ አስጠያፊ ነው። ሴቶችንም በወር አበባ ጊዜ ራቋቸው። ንጹሕ እስከሚሆኑም ድረስ አትቅረቡዋቸው።" [አል'በቀራ፡ 222] አላህ ከሴቷ ጋ ለሚደረግ ህጋዊ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ከመፈጸም የሚከለክለውን ምክንያት በሐይዷ (በወር አበባ) ወቅት ንጹህ አለመሆኗን እንደሆነ ግልጽ አድርጓል። የወር አበባን መጨረሻ ጊዜንም አንድ ቀን ከነ ሌቱት ወይም ሦስት ቀናት አልያም አስራ አምስት ቀናት አላደረገውም። ይህም ከላይ እንደተገለጸው አላህ (ከግብረ ስጋ ግንኙነት የመታቀብ) ፍርዱን የሰጠበት ምክንያት ከሐይድ (የወር አበባ) መከሰት ወይም አለመከሰት (ከወር አበባ መንጻቷ) ጋር በተያያዘ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ነው። በመሆኑም የወር አበባዋ እስካለ ድረስ ፍርዱም የፀና ይሆናል ማለት ነው (የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ይከለከላል)። ከወር አበባ ስትጠራ ደግሞ ፍርዱ ይነሳል (የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ይፈቀዳል)። ሁለተኛው ማስረጃ፦ በሰሒሕ ሙስሊም ኪታብ ትክክለኛ በሆነ ሐዲሥ እንደተዘገበው ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እናታችን ዓኢሻ ለዑምራ ኢሕራም አድርጋ ባለችበት ወቅት የወር አበባዋ መጥቶባት እንዲህ ብለዋታል፦ "ከወር አበባሽ እስክትፀጂ የአላህን ቤት (ካዕባ) ጠዋፍ እንዳታደርጊ፤ ከዛ ውጪ ሐጃጆች የሚፈፅሙትን ሁሉ ፈፅሚ።" እናታችን ዓኢሻ፦ "ከወር አበባ ንፁህ የሆንኩት በነሕር ቀን (እንስሳት መስዋዕት በሚደረጉበት፡ ዙልሒጃ 10ኛ ቀን) ነው።" ብላለች። በቡኻሪይ እና ሙስሊም እንደተዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ለእናታችን ዓኢሻ እንዲህ ብለዋታል፦ "ከወር አበባሽ ንፁህ እስክትሆኚ ድረስ ቆዪና ንፁህ ስትሆኚ ወደ አት'ተንዒም (መካ ውስጥ ወደሚገኝ ቦታ) ትሄጃለሽ።" ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እናታችን ዓኢሻን (አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸው) የሐጅን ሥርዓት ከማከናወን የከለከሉበትን ምክንያት የንጽህናዋ ጉዳይ እንጂ የወር አበባዋን በጊዜ ገደብ አላደረጉትም። ይህም የሚያመላክተን የዚህ ጉዳይ ፍርድ ቁርኝቱ ከወር አበባ ደም መኖር እና አለመኖር ጋ የተያያዘ መሆኑን ነው።
ሦስተኛው ማስረጃ፦ እነዚህ የወር አበባ ሊሚጀምርበት የሚችለውንና የሚያልቅበትን ክፍለ ጊዜና ዝርዝር የጊዜ ገደብ ምንም እንኳ ከፊቂህ ሊቃውንቶች መካከል ገድበው ያስቀመጡት ቢኖሩም መሰረታቸው ግን ቁርኣን አልያም ሓዲሥ አይደለም። ጉዳዩ ብዙዎችን የሚመለከት አሳሳቢ ጉዳይ ከመሆኑም ጋር በቁርኣንና በሓዲሥ ግን የተቀመጠለት ገደብ የለም። ይህ የጊዜ ገደብ ማስቀመጡን የአላህ ባሪያዎች በመገንዘብ አላህን የሚያመልኩበት ጉዳይ ቢሆን ኖሮ አላህ እና መልእክተኛው (የአላህ ሰላት እና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ለሁሉም ግልጽ በሆነ ሁኔታ ባብራሩት ነበር። ምክንያቱም እርሱን ተከትለው ለሚመጡ የሰላት፣ የጾም፣ የጋብቻ፣ የፍቺ፣ የውርስ እና ሌሎችም ህግጋት እጅግ አሳሳቢ ነውና። አላህ እና መልእክተኛው የሰላት ብዛትን፣ ወቅታቸውን፣ ሩኩዓቸውን እና ሱጁዳቸውን በግልጽ እንዳስቀመጡት ሁሉ። ዘካንም የሀብት መጠኑን፣ ዝቅተኛውን ዘካ የሚወጣበትን መጠን እና ዘካን የሚቀበሉ ሰዎችን በተመለከተ እንዳብራሩት፤ ፆምንም የቆይታ ጊዜውን እና ወቅቱን በተመለከተ እንዳብራሩት፤ ሐጅንም ከነዚህ ውጪ ያሉትንም ህግጋቶችንም በተመለከተ፤ ሌላው ቀርቶ የመብላት፣ የመጠጣት፣ የመተኛት፣ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት፣ የመቀመጥ፣ ወደ ቤት የመግባት እና የመውጣት ስርዓትን፤ እንዲሁም የመፀዳዳት ስርዓትን፤ በኢስቲጀማር ጊዜ (ስንፀዳዳ) የምንጠቀመውን የድንጋይ ብዛት እና የመሳሰሉትን እንኳን ሳይቀር ከጥቃቅን እስከ ትልቅ ያሉ ጉዳዮችን፤ አላህ የእስልምና ሃይማኖትን ምሉእ ያደረገበትን እና ፀጋውንም በምእመናን ላይ የሞላበትን ሁሉ እንዳብራሩት ይህንንም ባብራሩ ነበር። የበላይ የሆነው አላህ እንዳለው፦ "መጽሐፉንም ለሁሉ ነገር አብራሪ ሆኖ ባንተ ላይ አወረድነው።" [አን'ነሕል፡ 89] የበላይ የሆነው አላህ እንዲህ ብሏል፦ "(ይህ ቁርኣን) የሚቀጣጠፍ ወሬ አይደለም። ግን ያንን በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ለነገርም ሁሉ ገላጭ ነው።" [ዩሱፍ፡ 111] እነዚህ የወር አበባ ክፍለ_ጊዜዎች እና ዝርዝሮች በአላህ መጽሐፍም (ቁርኣን) ሆነ በአላህ መልእክተኛ ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ሱና ውስጥ እስካልተገኙ ድረስ በእነሱ ላይ የሚንጠለጠል ህግ እንደሌለ ግልፅ ሆነ። ይልቁኑ ትክክለኛው የህግጋቱ

መንጠልጠያ የሚወሰነው የወር አበባ ደም በመኖሩ እና ባለመኖሩ ላይ ነው ማለት ነው። ይህ ማስረጃ ደግሞ - ማለቴ፡- ፍርዱ (ብይኑ) በአላህ መጽሐፍ (ቁርኣን) እና በሱና አለመጠቀሱ ግምት ውስጥ የማይገባ ለመሆኑ አስረጅ መሆኑ - በዚህም ሆነ በሌሎች የዕውቀት ጉዳዮች የሚጠቅም መርህ ነው። ምክንያቱም ሸሪዓዊ ብያኔዎች ከአላህ ኪታብ (ቁርኣን) ወይም ከመልዕክተኛው ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ሱና በተገኘ ማስረጃ ወይም ከታወቀ ዑለሞች የጋራ ስምምነት (ኢጅማዕ) ወይም ከትክክለኛ ቂያስ (ተመሳሳይነት) መሰረት በማድረግ ካልሆነ በስተቀር የማይመሰረት በመሆኑ ነው። ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ አንድ መሰረታዊ መርህን በተመለከተ እንዲህ ብለዋል፡- "ከነዚህም መካከል አላህ በቁርኣንና በሱና ብዙ ፍርዶችን ያቆራኘበት የሆነው ሓይድ ብለን የምንጠራው ስም የቆይታ ጊዜውን ማወቁ ለህብረተሰቡ አስፈላጊና አሳሳቢ ከመሆኑም ጋ ቢያንስ ወይም ቢበዛ ሊኖረው የሚችለውን ቀነ ገደብ እንዲሁም በሁለት የወር አበባ ጊዜያት መካከል ንጹህ ሆነው የሚቆዩበትን የጊዜ ገደብ ተወስኖ አልተቀመጠም። በቋንቋ ደረጃም ቢሆን በተለያዩ የሐይድ ጊዜ ገደቦች መካከል የተለያየ አገላለፅ የለም። በመሆኑም የሓይድን የጊዜ ገደብ ወስኖ ያስቀመጠ ሰው ቁርኣንና ሱናን ተቃርኗል።" ንግግራቸው እዚህ አበቃ። አራተኛው ማስረጃ፦ ተጨባጩን ማስተዋል፦ ማለትም: የተስተካከለ ትክክለኛ ቂያስ: የበላይ የሆነው አምላክ አላህ የወር አበባን (አስከትሎ ለሚያመጣቸው ፍርዶች) አስቸጋሪነቱን እንደ ምክንያትነት አስቀምጧል። በመሆኑም የወር አበባ በሚከሰትበት ጊዜ ሁሉ አስቸጋሪነቱም አብሮት አለ፤ አስቸጋሪ ለመሆኑ በሁለተኛውና በአንደኛው ቀን ወይም በአራተኛውና በሦስተኛው ቀን መካከል ምንም ልዩነት የለም ማለት ነው፤ በአሥራ ስድስተኛው እና በአሥራ አምስተኛው ቀን መካከልም ይሁን በአሥራ ስምንተኛው እና በአሥራ ሰባተኛው ቀን መካከል ምንም ልዩነት የለም ማለት ነው። ስለዚህም የወር አበባው ያው የወር አበባ እስከሆነ ድረስ አስቸጋሪነቱም ያው አስቸጋሪነት ነው። በመሆኑም ህግጋቱን ያስፈረደው ምክንያትም በሁለቱም ቀናት ተመሳሳይ ነው። ታዲያ በ(ሚያስፈርደው) ምክንያት ተመሳሳይ ሆነው ሳለ የሁለቱን ቀናት ፍርድ መለያየት እንዴት ትክክል ሊሆን ይችላል? ይህ ታዲያ ትክክለኛውን ቂያስ የሚቃረን አይደለምን? በትክክለኛ ቂያስ (ሲመዘኑ) ሁለቱ ቀናቶች በ (ሚያስፈርደው\ በሚያስይዘው) ምክንያት ተመሳሳይ እስከሆኑ ድረስ በፍርድም ተመሳሳይ ይሆኑ አይደለምንም?

አምስተኛው ማስረጃ፦ ገደብ ያስቀመጡ የፊቂህ ሊቃውንቶች መካከል የቃላቸው መለያየትና መጣረስ፤ ይህ የሚያመለክተው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል በቂ መነሻ አለመኖሩን ነው። ይልቁኑ መነሻው ስህተት ወይም ትክክል ሊሆን የሚችልበት የኢጅቲሃድ ብይን ነው ማለት ነው። በዚህም አንዳቸው ከሌላኛው ይልቅ ሊከተሉት ይበልጥ የተገባ ሸሪዓዊ መመዘኛ አይኖርም። ባልተግባቡበት ጉዳይ መመለሻው ደግሞ ወደ ቁርኣን እና ሐዲሥ ነው።

ቢያንስ ወይም ቢበዛ ሊኖር የሚችለውን የወር አበባ የጊዜ ገደብ የለም የሚለው ቃል ጠንካራና አመዛኙ አቋም መሆኑ ግልፅ እስከሆነ ድረስ ያለ ምንም የዕድሜም ሆነ የቆይታ ግዜ ገደብ ሴት ልጅ በቁስል ወይም በመሳሰሉት ምክንያቶች ሳይሆን እንዲሁ በተፈጥሮ የምታየው ደም ሁሉ የወር አበባ ደም ነው ማለት ነው። ነገር ግን ያለምንም ማቋረጥ ወይም ለጥቂት ግዜያት ለምሳሌ በወር ውስጥ ለአንድ ወይም ለሁለት ቀናት ብቻ ንጹህ የምትሆን ከሆነ ግን ይህ የሚፈሳት ደም “ኢስቲሓዷህ” ይባላል። በአላህ ፈቃድ የኢስቲሓዷህ ማብራሪያ እና ብይኖቹን በተመለከተ ወደፊት ይቀርባል። ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ እንዲህ ብለዋል፡- ከማህፀን የሚወጣ ነገር ሁሉ ኢስቲሓዷህ ለመሆኑ ማስረጃ እስካልተገኘለት ድረስ በመሰረታዊ መርሆው የወር አበባ ነው። እንዲህም ብለዋል፦ (ከማህፀን) የሚፈስ ደም በደም ሥር መጎዳት ወይም በቁስል ምክንያት መሆኑ እስካልታወቀ ድረስ የወር አበባ ነው። ይህ አባባል ከማስረጃ አንፃር እጅግ በጣም ትክክለኛ እንደሆነው ሁሉ ለመረዳትና ለመገንዘብም በጣም የቀረበ ነው። ለመሥራት እና ተግባራዊ ለማድረግም እንዲሁ በጊዜ ገድበው ከጠቀሱት ይልቅ ይበልጥ የቀለለ ነው። እንደዚህ በመሆኑም ተቀባይነት ለማግኘት ይበልጥ የተገባ ይሆናል፤ ምክንያቱም ቀላል እና ገር ከሆነው የእስልምና ሃይማኖት መንፈስና መርሆ ጋ ስለሚስማማ ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፦ "በናንተም ላይ በሃይማኖቱ ውስጥ ምንም ችግር አላደረገባችሁም።" [አል'ሐጅ፡ 78] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብሏል፦ "ዲን (ሃይማኖት) ገር ነው፤ ማንም ሰው ዲንን አያከርም ዲኑ ቢያሸንፈው እንጂ፤ ስለዚህ ወደ ፍጽምና (ትክክለኝነት) ለመቅረብ ሞክሩ፤ አበስሩም።" (አል'ቡኻሪይ ዘግበውታል)

ከአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ስነምግባር መካከል፦ "በሁለት ጉዳዮች መካከል ምርጫ ከቀረበላቸው ኃጢአት እስካልሆነ ድረስ ከሁለቱ ቀላል የሆነውን ይመርጡ ነበር።"

የእርጉዝ ሴት የወር አበባ፦

ብዙውን ጊዜ አንዲት ሴት ካረገዘች የወር አበአባ ደም ከእርሷ ይቆማል። ኢማም አሕመድ (አላህ ይዘንላቸውና) እንዲህ ብለዋል፡- "ሴቶች ማርገዛቸውን የሚያውቁት የወር አበባ ደማቸው ሲቋረጥ ነው።" ነፍሰ ጡር ሴት ከመውለዷ ከጥቂት ጊዜ ለምሳሌ ከሁለት ወይም ከሦስት ቀናት በፊት ሆኖ በዛ ላይ ህመም ያለበት ደም ከፈሰሳት ይህ የድህረ ወሊድ ደም ነው። ከመውለዷ በፊት ረጅም ጊዜ ወይም ከመውለዷ ጥቂት ጊዜ ቀደም ብሎ ከሆነና ነገር ግን ከእሱ ጋር ህመም የሌለበት ከሆነ ኒፋስ (የድህረ ወሊድ ደም) አይባልም። ታዲያ ይህ ደም የወር አበባ ህግጋት የሚፀናበት የወር አበባ ደም ነውን? ወይስ የወር አበባ ህግጋት የማይመለከተው ብልሹ ደም ነው?

በዚህ ጉዳይ በዑለሞች መካከል የሃሳብ ልዩነት አለ። ትክክለኛው አቋም እንደተለመደው በወር አበባዋ ወቅት የሚፈስ ከሆነ የወር አበባ ነው፤ ምክንያቱም ሴት የሚገጥማትን ደም በተመለከተ መሠረታዊው መርህ የወር አበባ ደም ከመሆን የሚያቅብ ምክንያት እስካልተገኘ ድረስ የወር አበባ ደም መሆኑ ነውና። ነፍሰ ጡር ሴት የወር አበባ አታይም ብሎ የሚያቅብ ማስረጃ ደግሞ በቁርኣንም በሐዲሥም ውስጥ የለም።

ይህ ደግሞ የኢማም ማሊክ እና የኢማም አሽ'ሻፊዒይ መዝሀብ (አቋም) ነው፤ የሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህም ምርጫ ይህው ነው፤ ኢኽቲያራት በሚባለው ኪታባቸው ላይ (ገጽ 30) እንዲህ ብለዋል፡- አል'በይሀቂይ ከአሕመድ በሪዋያ መልኩ ዘግበውታል። እንደውም ወደ እሱ የተመለሱበት አቋም እንደሆነም ነው የተናገሩት።

ከዚህም በመነሳት የነፍሰ ጡር ሴት የወር አበባዋ እርጉዝ እንዳልሆነችዋ ሴት መሆኑ የተረጋገጠ ነው፤ ከሁለት ጉዳዮች በስተቀር፡-

የመጀመሪያው ጉዳይ፦ ፍቺ፤ እርጉዝ ያልሆነች የወር አበባዋን መጠባበቅ (ዒዳ) ያለባትን ሴት መፍታት ክልክል ነው። ለነፍሰ ጡር ሴት ግን የተከለከለ አይደለም። ምክንያቱም እርጉዝ ያልሆነችን ሴት በወር አበባ ጊዜዋ መፍታት ተከታዩን የበላይ የሆነውን አምላክ አላህ ቃልን ይቃረናልና፡- "ለዒዳቸው የተመቻቹ ሲሆኑ ፍቱዋቸው።" [አጥ'ጠላቅ፡ 1] ነፍሰ ጡር የሆነችን ሴት በወር አበባ ጊዜዋ ሳለች መፍታት ግን ከፍ ብለን ከጠቀስነው አንቀፅ ጋር የሚቃረን አይደለም፤ ምክንያቱም ነፍሰ ጡር ሴትን የሚፈታ ሰው የወር

አበባዋን አየችም አላየችም ለዒዳዋ የተመቻቸች ሆና ነውና የፈታት። ምክንያቱም ዒዳዋ (ለመፈታት የምትጠብቀው ጊዜዋ) እርጉዝ መሆኗን ነበር። ስለዚህም ነው ከሌሎቹ ሴቶች በተለየ መልኩ ከጾታዊ ግንኙነት በኋላ መፍታትን የማይከለከለው። ሁለተኛው ጉዳይ፦ የወር አበባ ከሚያዩ ሌሎች ሴቶች በተለየ መልኩ የነፍሰጡር ሴት የወር አበባዋ ዒዳ አይቋጭበትም። ምክንያቱም ነፍሰ ጡር የሆነች ሴት የወር አበባ አየችም አላየችም እስካልወለደች ድረስ ዒዳዋ አያበቃምና። አላህ እንዲህ ብሏልና፦ "የእርግዝና ባለቤቶችም ጊዜያቸው ጽንሳቸውን መውለድ ነው።" [አጥ'ጠላቅ፡ 4]

*

# ክፍል ሦስት: የወር አበባ መዛባትን በተመለከተ

የወር አበባ መዛባት የተለያየ ዓይነት አለው፡-

የመጀመሪያው ዓይነት፦ መጨመር ወይም መቀነስ፤ ለምሳሌ የሴቷ የወር እበባ ቀናት ልማድ ለስድስት ቀናት ይሆንና ደሟ እስከሰባተኛው ቀን ድረስ ይዘልቃል፤ ወይም ልማዷ እስከ ሰባት ቀን ድረስ ይሆንና በስድስተኛው ቀን ንጹህ የምትሆንበት ሁኔታ አለ።

ሁለተኛው ዓይነት፦ ቀድሞ መምጣት ወይም መዘግየት፤ ለምሳሌ የወር አበባ ልምዷ በወሩ መገባደጃ ላይ ይሆንና (ነገር ግን) የወር አበባ በወሩ መጀመሪያ ላይ ብትመለከት፤ ወይም ልማዷ በወሩ መጀመሪያ ላይ ይሆንና በወሩ መጨረሻ ላይ የምታይበት ሁኔታ።

እነዚህ ሁለት ዓይነቶች ያላቸውን ብይን በተመለከተ በኢስላም ሊቃውንት መካከል የሀሳብ ልዩነት ያለ ሲሆን ሚዛን የሚደፋው አቋም ከተለምዶ ጊዜዋ ይብዛም ይነስ ከሚመጣበትም ጊዜም ይቅደም ይዘግይ ደም እስካየች ድረስ የወር አበባ ነው ከእርሱ በነጻች ጊዜ ደግሞ ንፁህ ትሆናለች የሚለው ነው። ለዚህም ማስረጃው ከዚህ ቀደም ብለን ባሳለፍነው ምዕራፍ ጠቅሰናል፤ ሕጉ ያወጣው (አምላካችን አላህ) የወር አበባ ድንጋጌዎች የወር አበባ መገኘት አለመገኘቱ ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው ብለናል። ይህ ደግሞ የኢማሙ ሻፊዒይ መዝሀብ እና የሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ ምርጫም ነው። የሙግኒ ኪታብ አዘጋጅም እንዲህ ብለው ሀሳቡን ደግፈው አጠናክረውታል፦ አንዳንድ መዝሀቦች ላይ በተጠቀሰው መልኩ ልማዷ ቦታ የሚሰጠው ቢሆን ኖሮ ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ለህዝባቸው ባብራሩት ነበር፤ ማብራሪያውንም ሊያስቀሩ የሚቻላቸው አይደሉም። ማብራሪያውን ከጊዜው ማዘግየት አይቻልምና፤ ሚስቶቻቸውም ሌሎች ሴቶችም የዚህን ማብራሪያው ሁሌም የሚያስፈልጋቸው ናቸው፤ በመሆኑም (ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን)) ይህን ጉዳይ ከማብራራት ችላ አይሉትም ነበር፤ የሴት ልጅ የደም ፍሰት ልማዷንም ይሁን ማብራሪያውንም በተመለከተ ከነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን የመጣው ኢስቲሓዷ ላይ ስላለች ሴት እንጂ ሓይድ ላይ ስላለች ሴት አይደለም። ሦስተኛው ዓይነት፦ ቢጫ ወይም ቡናማ ቀለም ያለው ሆኖ ደሙ ከቁስሎች እንደሚወጣው ፈሳሽ ቢጫ ነገር ወይም በቢጫ እና በጥቁር መካከል ቡናማ ቀለም ያለውን ፈሳሽ ታያለች። (ይህ የተከሰተው) በወር አበባ ጊዜ ወይም ከመንጻቷ በፊት ከወር አበባዋ ጋር ተቆራኝቶ የፈሰሳት ከሆነ የወር አበባ ነውና የወር አበባን ብይን እናፀድቅለታለን፤ ከንጽህናዋ በኋላ ያጋጠማት ከሆነ ግን የወር አበባ አይደለም። ኡሙ ዐጢያህ (አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላት) እንዲህ ስላለች፡- "ከወር አበባ ከጠራን በኋላ የሚከሰትብንን ቢጫ ወይም ቡናማ ነገር ከምንም አንቆጥረውም ነበር።" አቡ ዳውድ ሰሒሕ በሆነ ሰነድ ዘግበውታል። ቡኻሪም "ከወር አበባ ከጠራን በኋላ" የሚለውን ሳይጨምሩ ዘግበውታል። ነገር ግን ይህን ሐዲሥ የጠቀሱበትን ምዕራፍ፦ "ከወር አበባ ውጭ ባሉት ቀናት ቢጫ እና ቡናማ ቀለም ያለውን ፈሳሽ በተመለከተ የመጣ ባብ" ብለው ርእስ ቋጥረውለታል። የቡኻሪ ማብራሪያ በሆነው ፈትሑል ባሪ ኪታባቸው ላይ ደግሞ እንዲህ ብለዋል፦ "ይህ የሚያመለክተው ቀደም ሲል ያሳለፍነውን የዓኢሻን፡- 'ነጩን ፈሳሽ እስክታዩ ድረስ።' የሚለውን ሐዲሥ ነው። በርእሰ ጉዳዩ የተጠቀሰው የኡሙ ዐጢያህ ሐዲሥ ያ - በዓኢሻ ሐዲሥ - የተባለው ማለትም ቢጫ ወይም ቡናማ ፈሳሽ የተመለከተችው በወር አበባ ጊዜዋ ከሆነ እንደ ወር አበባ ተደርጎ እንደሚቆጠር ሲሆን ከወር አበባ ጊዜዋ በኋላ ያየችው ከሆነ ደግሞ ኡሙ ዐጢያ እንዳሉት እንደሚሆን ነው።" ንግግራቸው እዚሁ አበቃ። ሸይኹ አሁን የዓኢሻ ሐዲሥ ብለው የጠቀሱት ሓዲሥ ቡኻሪይ ከዚሁ ምዕራፍ በፊት ጀዝም አድርገው ያለሰነድ የዘገቡትን ሓዲሥ ነው። ሴቶች ወደ እናታችን ዓኢሻ ቢጫማ የወር አበባ ደም ያለበትን ጥጥና "ዱርጀህ" (አንዲት ሴት የወር አበባ መኖሩን ለማወቅ የምትለብሰው ነገር) አንድ ላይ አድርገው ይልኩባትና የወር አበባ ማብቃት አለማብቃቱን ይጠይቋት ነበር። እርሷም "ቀስሰተል በይዳእ" ማለትም "ነጣ ያለውን ፈሳሽ እስክታዩ ድረስ አትቻኮሉ" ትላቸው ነበር። ነጩ ፈሳሽ የተባለው የወር አበባ በሚያበቃበት ጊዜ ማህፀን የሚተፋውን ነጭ ፈሳሽ ነው።

አራተኛው ዓይነት፦ የወር አበባዋ መቆራረጥ፤ ማለትም አንድ ቀን የወር አበባ ደም አይታ በቀጣዩ ቀን ደግሞ ትነፃለች፤ እነዚህን መሰል ሁኔታዎች ሁለት ዓይነት አላቸው፦

የመጀመሪያው ሁኔታ፦ ይህ ሴቷ ሁል ጊዜ በዘውታሪነት ደም ለሚፈሳት አይነቷ ነው። ይህ የኢስቲሓዷ ደም ነው የሚባለው፤ ይህ ሁኔታ ያጋጠማትም ብይኗ የኢስቲሓዷ ደም እንዳጋጠማት ነው።

ሁለተኛው ሁኔታ፦ ሴቷ በዘውታሪነት ደም አይፈሳትም ይልቁኑ ደሙ ለተወሰነ ግዜ ነው የሚመጣባት፤ መሀል ላይም ትክክለኛ የመንጻት ጊዜ ይኖራታል። ይህንን የንፅህና ወቅት በተመለከተ ዑለሞች አላህ ይዘንላቸውና የንፅህና ወቅት ነው? ወይንስ የወር አበባ ብይን የሚመለከተው ወቅት ነው? በሚለው ላይ የሀሳብ ልዩነት አለባቸው።

በዚህ ረገድ የሻፊዒይ መዝሀብ ከሁለቱ አባባሎች በጣም ትክክለኛ በሆነው አቋማቸው የወር አበባን የተመለከቱ ብይኖች በዚህ ላይ ተፈጻሚነት እንዳላቸው ገልፀዋል። ስለዚህም የወር አበባ ተደርጎ ይቆጠራል ማለት። ይህም የሸይኹል-ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ እና የአል-ፋኢቅ ኪታብ አዘጋጅ ምርጫ ነው፤ የአቡ ሐኒፋ መዝሀብም ይህው ነው። ይህም የሆነው ነጩ ፈሳሽ በዚህ ወቅት ስለማይታይ ነው፤ ምክንያቱም በሁለቱ ቀናት መካከል ያለውን ሓይድ የማይመጣባትን ቀን ጡህራ ናት ካልን ከሓይዱ ንፁህ ከሆነችበት ቀን በፊት ለአንድ ቀን ሓይድ ላይ ሆና ንፁህ ከሆነችበት በኋላ ባለው ቀንም ሓይድ ላይ ትሆናለች እያልን ነው። እንዲህ የሚል ደግሞ የለም። ምክንያቱም እንዲህ የምንል ከሆነ በቁርእ (በወር አበባ) ዒዳዋን የምትጠባበቅ ሴት በአምስት ቀናት ውስጥ ዒዳዋን ትጨርሳለች ማለት ይሆንብን ነበር። ምክንያቱም ይህ ቀን ንፁህ ነች ካልን በየሁለት ቀኑ በመታጠብ እና በሌሎችም ነገሮች በሴቶቹ ላይ ድካምና እና አስቸጋሪነትን መፍጠር ነው። በዚህ ሸሪዓ ውስጥ ደግሞ አስቸጋሪነት የለም። ምስጋና ሁሉ ለአላህ የተገባ ነው።

በሌላ በኩል ከሓንበሊ አስተምህሮ ይበልጥ የተሰራጨ በሆነው ደግሞ የደም ፍሰቱ ሐይድ ሲሆን ንፁህ የሆነችበት ቀን ደግሞ "ጡሀራ" ነው የሚል ነው። የሐይድ እና የንፅህና ጥምር ጊዜ ረዥሙን የሐይድ ጊዜ ወሰን ካለፈ ግን ከዚህ ገደብ በላይ ያለው የደም ፍሰት እንደ ኢስቲሓዷህ የሚቆጠር ይሆናል።
የአል-ሙግኒይ አዘጋጅ (የሐንበሊይ ፊቅህ ትልቅ የማመሳከሪያ መጽሐፍ ነው) እንዲህ ብለዋል፦ "ደሙ ከአንድ ቀን በፊት ሙሉ ካቆመ ንፁህ ተደርጎ አይታሰብም። " ስለ ድህረ ወሊድ ባለው ሁኔታ ላይ በጠቀስነው መሰረት ከአንድ ቀን በታች ላለው ትኩረት የሚሰጠው አይሆንም። ይህም ነው ትክክለኛው አቋም - ኢንሻአሏህ - ። ምክንያቱም ደሙ አንድ ጊዜ ይፈስና ሌላ ጊዜ ደግሞ ይቋረጣል። በየሰአቱ እንዲታጠቡ ማስገደድ ደግሞ ሊወገድ የሚገባውን ችግር ያቀፈ ነው። አላህ እንዲህ ብሏልና፦ "በናንተም ላይ በሃይማኖቱ ውስጥ ምንም ችግር አላደረገባችሁም።" [አል'ሐጅ፡ 78] (አስከትለውም) እንዲህ አሉ፦ "ስለሆነም ግልጽ ማስረጃ ካላየች በስተቀር ደሙ ከአንድ ቀን ባነሰ ጊዜ ውስጥ ከቆመ "ጠሀራ" ተብሎ ሊወሰድ አይችልም። ለምሳሌ የወር አበባዋ መጨረሻ ጊዜዋ ላይ ፍሰቱ ከቆመ ወይም ነጭን ፈሳሽ ካየች ነው።" ንግግራቸው እዚሁ አበቃ።
ስለዚህ የሙግኒይ አዘጋጅ አባባል በሁለቱ አባባሎች መካከል ሚዛናዊው አቋም ነው። ትክክለኛውን ነገር የሚያውቀው አሏህ ነው።
አምስተኛው ዓይነት:- የደም ድርቀት: ማለትም ሴቷ የሆነ እርጥብ ፈሳሽ ነገርን ታያለች። ይህ በሐይድ ጊዜ ወይም ከሱ ጋ የተያያዘ ከመተጣጠቧ በፊት ያየችው ከሆነ የወር አበባ (ሐይድ) ነው። ጨርሻለሁ ብላ ከተጣጠበች በኋላ የተከሰተ ከሆነ ግን ሐይድ አይደለም። ምክንያቱም ገፋ ቢል የቢጫ እና ጥቁር ቡናማ አይነቱ ፈሳሽ መሰል ቢሆን ነው፤ የእሱ ብይን ደግሞ ይህው ነው።

*

# ክፍል አራት፦ የወር አበባን የተመለከቱ ሕግጋቶች

የወር አበባን የተመለከቱ ህግጋት ብዙ ናቸው፤ ከህያም ይበልጣሉ። ከእነርሱ ውስጥ እጅግ አሳሳቢ የሆኑትን እንጠቅሳለን፦
የመጀመርያው ሶላት፦ በወር አበባ ላይ ላለች ሴት የግዴታም ሆነ የሱና ሶላቶችን መስገዷ የተከለከለ ነው። ብትሰግድም ተቀባይነትም የለውም። ምናልባት ንፁህ በሆነችበት ጊዜ አንድ ረከዓ ሙሉውን ልትሰግድ የምትችልበትን ያህል ግዜ አግኝታ እስካልሆነ ድረስ ሶላት ግዴታ አይሆንባትም፤ ያ ንፁህ በሆነችበት ወቅት ያገኘችው ከሶላቱ የመጀመሪያው ሰዓት ላይም ሆነ የመጨረሻው ግዜ ላይ እስካገኘች ድረስ መስገዱ ግዴታ ይሆንባታል።
ከመጀመርያው ወቅት ያገኘች ስንል ለምሳሌ፦ አንዲት ሴት ጀንበር ከጠለቀች በኋላ አንዲት ረከዓ እንኳ ሊያሰግዳት ከሚችልበት ቆይታ በኃላ የወር አበባዋ ቢመጣ ከወር አበባዋ ስትጠራ ያኔ ያለፋትን የመግሪብ ሶላት ማካካስ (ቀዷ ማውጣት) አለባት፤ ምክንያቱም የወር አበባዋ ከመምጣቱ በፊት አንድ ረከዓም ቢሆን መስገድ የምትችልበትን ግዜ አግኝታ ነበረችና ነው።
ከመጨረሻው ወቅት ያገኘች ስንል ደግሞ ለምሳሌ፦ ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት የፈጅርን ሶላት አንድ ረከዓ መስገድ የምትችልበት ጊዜ አግኝታ ከወር አበባዋ የጸዳች እንደሁ የፈጅርን ሰላት ማካካስ (ቀዷ ማውጣት) አለባት። ምክንያቱም አንዲት ረከዓን ለመስገድ የሚያስችላትን ግዜ አግኝታለችና ነው።
በወር አበባ ላይ ያለችው ሴት ያገኘችው ወቅት አንድ ሙሉ ረከዓ እንኳ ለመስገድ የሚያስችላት ካልሆነ ደግሞ፤ እንደምሳሌ ለመጀመሪያው ልክ ጀንበር እንደጠለቀች ወዲያው የወር አበባ ብታይ ወይም በሁለተኛው ምሳሌ ላይ ካየነው ፀሐይ ከመውጣቷ (አንድ ረከዓ እንኳ ልትሰግድ በማትችልበት ልክ)ቀደም ብሎ ንፁህ ብትሆን ሶላት መስገድ ግዴታ አይሆንባትም፤ ምክንያቱም ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋልና፦ "የሶላትን አንድ ረከዓ ያገኘ ሰው ሙሉ ሶላቱን አግኝቷል።" (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል) መልዕክቱ በተዘዋዋሪ የሚያስገነዝበን ከአንድ ረከዓ በታች ያገኘ ሰው ሶላትን አላገኘም ማለት ነው።
የዐስር ሶላትን ወቅት አንድ ረከዓ ካገኘች ከዐስር ሶላት ጋ የዙሁር ሶላትንም መስገድ ግዴታ ይሆንባታልን? ወይም የዒሻ ሶላትን የመጨረሻ ወቅት አንድ ረከዓ ካገኘች ከዒሻእ ሶላት ጋ የመግሪብም ሶላትንም ልትሰግድ ግዴታ ይሆንባታልን?
በዚህ ጉዳይ ላይ ዑለሞች ልዩነት አሳይተዋል፤ አመዛኙ አቋም ግዴታ የሚሆንባት ወቅቱን ያገኘችበት ሶላት መስገድ ብቻ ነው፤ ይህም ማለት ከላይ ባየነው ምሳሌ መሰረት ግዴታ የሚሆንባት የዐስር እና የዒሻእ ሶላት ብቻ ነው። ምክንያቱም ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋልና ነው፦ "ፀሀይ ከመጥለቋ በፊት የዐስር ሶላትን አንድ ረከዓ ያገኘ ሰው የዐስርን ሶላት አግኝቷል።" (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል) ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ዙሁር እና ዐስር አግኝቷል አይደለም ያሉት። ዙሁር መስገድ ግዴታ መሆኑን አያይዘው አልጠቀሱም፤ መሰረታዊ እውነታው ደግሞ ከግዳጅ ንፁህ መሆን ነው። ይህ የአቡ ሐኒፋ እና ማሊክ መዝሀብ (አቋም) እንደሆነ ሸርሕ አል-ሙሀዘብ በተሰኘው ድርሳን ላይ ተወስቷል። ዚክር ማድረግ (አላህን ማወደስ)፣ ተክቢራ (አላሁ አክበር ማለት)፣ ሱብሐነላህ አልሐምዱሊላህ ማለት፣ ለምግብ እና ለሌሎች ነገሮችን ቢስሚላህ ማለት፣ ሐዲሥ እና ፊቅህ ማንበብ፣ ዱዓ ማድረግና ለዱዓ አሚን ማለት እንዲሁም ቁርኣንን ማዳመጥ መሰል ነገራቶች አንዱም ቢሆን እርም (ሐራም) አይሆንባትም። በቡኻሪይ እና ሙስሊም እንዲሁም በሌሎች መዛግብት ላይ በተረጋገጠ ሰነድ እንደተዘገበው፦ "ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በዓኢሻ (ረዲየላሁ ዐንሀ) በወር አበባ ላይ ሆና ጭኗ ላይ ተደግፈው ቁርኣን ይቀሩ ነበር። እንዲሁም በቡኻሪይ እና ሙስሊም እንደተዘገበው ኡሙ ዐጢያህ (አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና) ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) የሚከተለውን ሲናገሩ ሰምቻለሁ ብላለች፦ "ለሁለቱ የዒድ ሶላቶች መልካም ነገሮችን እንዲመለከቱና የሙእሚኖችን ዱዓ እንዲካፈሉ ልጃገረዶች፣ በጫጉላ ውስጥ የሆኑና የወር አበባ ላይ ያሉ ሴቶችም (ወደ መስገጃው ቦታ) ይወጣሉ። የወር አበባ ላይ ያሉ እንስቶች ግን ከመስገጃ ስፍራው ራቅ ይበሉ (ብለው አዘዋል)።" በወር አበባ ላይ ያለች ሴት ራሷ ቁርኣንን ማንበቧን በተመለከተ ግን በዓይን በማየት ብቻ ወይም ምላሷን ሳታንቀሳቅስ በልቧ ብቻ ለምሳሌ ቁርኣን ወይም ሉሕ በማስቀመጥ የቁርኣን አንቀጾችን እየተመለከተች በልቧ መቅራቷ ምንም ችግር የለበትም። አን'ነወዊይ የአልሙሀዙብን ባብራሩበት እንዲህ ብለዋል፦ "ያለ (ምንም የዑለማዎች) ልዩነት የተፈቀደ ነው።" የምትቀራው ምላሷን እያንቀሳቀሰች ከሆነ ግን ብዙሃኑ ዑለሞች የተከለከለ ነው፤ አይፈቀድም የሚል አቋም አላቸው። አል'ቡኻሪይ፣ ኢብኑ ጀሪር አጥ'ጠበሪይ እና ኢብኑል ሙንዚር የተፈቀደ ነው ብለዋል። ከኢማሙ ማሊክ እና በቀደመ አቋማቸው ከኢማሙ አሽሻፊዒይም እንደተላለፈ ፈትሑል ባሪ ላይ አስፍረዋል፤ እንዲሁም አል-ቡኻሪይም ከኢብራሂም አን-ነኽዒይ እንዳስተላለፉት፦ “የቁርኣን አንቀፅ መቅራት ምንም ችግር የለበትም።” ብለዋል። ሸይኹ ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ ኢብኑ ቃሲም ተሕቂቅ ባደረጉት የመጅሙዕ አል'ፈታዋ ኪታባቸው ላይ

እንዲህ ብለዋል፦ «በመሰረቱ ቁርኣንን ከመቅራት የሚከለክላት ሐዲሥ የለም። "ጀናባ ላይ ያለም ይሁን የወር አበባ ላይ ያለች ሴት እና ከቁርኣን ምንም አያንብብ።" የሚለው ሐዲሥ ዶዒፍ ሓዲሥ ነው። » የታወቁ የሐዲስ ሊቃውንት የተስማሙበት ደካማ ሐዲስ ነው። በነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ዘመን የነበሩ ሴቶች የወር አበባ ደም ያዩ ነበር። ቁርኣን ማንቡብ እንደ ሶላት በእነርሱ ላይ የተከለከለ ቢሆን ኖሮ ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ለሕዝባቸው ያብራሩት ነበር፤ የምእመናን እናቶችም ያስተምሩትና ለሰዎችም ያስተላልፉት ነበር። ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) መከልከላቸውን ያስተላለፈ አንድም ሱሓባ እስከሌለ ድረስ እሳቸው እንዳልከሉ እየታወቀ እርም ማድረግ ለማንም አይፈቀድለትም። በነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) የሕይወት ዘመን ብዛት ያላቸው የወር አበባ የሚያዩ ሴቶች እያሉ ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ካልከለከሉ እርም የተደረገ አለመሆኑን እንረዳለን።" ንግግራቸው እዚህ ጋ አበቃ።

የዑለማዎችን የሀሳብ መለያየት ግምት ውስጥ በማስገባት መባል ያለበት ነገር ቢኖር በወር አበባ ላይ ያለች ሴት ቁርአንን በምላስ (ቃላቱን ) አለመንበቧ የተሻለና በላጭ መሆኑን ነው። ነገር ግን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለምሳሌ አስተማሪ ከሆነች ተማሪዎቿን ለማስተማር ወይም ተፈታኝ ተማሪ ሆና በፈተና ጊዜ እና በመሳሰሉት ሁኔታዎች ወዘተ. ከሆነ ይቻላል።

ሁለተኛው: ፆም፦ የወር አበባ ላይ ያለች ሴት ላይ ግዴታም ሆነ ሱና ፆም መፆም እርም ነው። ተቀባይነትም አያገኝም፤ ነገር ግን (በወር አበባ ምክንያት ያመለጣትን) ግዴታ የሆነ ፆም ቀዷእ ማውጣት ግዴታ ይሆንባታል። ማስረጃውም ተከታዩ የእናታችን ዓኢሻ ሐዲሥ ነው፦ "በእኛ ላይ ይደርስብን ነበር - ማለትም፡ የወር አበባ - ፆምን በሌላ ጊዜ ቀዳእ እንድናወጣ እንታዘዝ ነበር ነገርግን ሶላትን ቀዳእ እንድናወጣ (እንድናካክስ) አልታዘዝንም።" (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ፆምኛ ሆና እያለ የወር አበባዋ ከመጣባት፤ ምንም እንኳን ፀሐይ ከመጥለቋ ከትንሽ ቅፅበት በፊት ቢሆን እንኳ ፆሟ ይበላሻል። ግዴታ ፆም ከሆነ ያንኑ ቀን ማካካስ (ቀዳእ ማውጣት) አለባት።

ነገር ግን ጀንበር ከመጥለቋ በፊት የወር አበባ እንደሚመጣባት በውስጧ ተሰምቷት ነገር ግን ደሙ የፈሰሳት ጀንበር ከጠለቀች በኋላ ከሆነ ሚዛናዊ በሆነው የዑለሞች አቋም መሰረት ፆሟ (ትክክል) ሙሉ ነው። ምክንያቱም በሆድ ውስጥ ያለ ደም ምንም ዓይነት ብያኔ (ሑክም) የለውምና። ምክንያቱም ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) በህልሟ አንድ ወንድ የሚያየውን ያየች ሴት ገላዋን የመታጠብ ግዴታ ይኖርባት እንደሁ በተጠየቁ ጊዜ: “ፈሳሽ ካየች አዎ።” ነበር ያሉት። በዚህም ብይኑን ያቆራኙት የዘር ፈሳሽ በማየት እንጂ በውስጧ በመዘዋወሩ አይደለም። በተመሳሳይ መልኩ የወር አበባ ወደ ውጭ በመታየት ካልሆነ በስተቀር በውስጧ በመዘዋወሩ ምክንያት ብይኖች ተፈፃሚ አይሆኑም።

በወር አበባ ላይ ሆና ጎህ ከቀደደም የዚያን ቀን ፆሟ ትክክል አይሆንም። ጎህ ከቀደደ በኋላ ወዲያውኑ ንፁህ ብትሆንም።

ጎህ ሊቀድ ሲል ንፁህ ከሆነችና ከፆመች ደግሞ ፆሟ ትክክለኛ ነው። ልክ እንደ ጀናባ ላይ የሆነ ሰው ጁኑብ ሆኖ ለመፆም አስቦ ጎህ ከቀደደ በኋላ ገላውን ቢታጠብ ፆሙ ትክክል እንደሚሆነው ሁሉ ሴቷም ገላዋን የታጠበችው ጎህ ከቀደደ በኋላ ቢሆንም ፆሟ ትክክል ይሆናል። እናታችን ዓኢሻ ያስተላለፈችው ሐዲሥ እንዲህ ስለሚል፦ "ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ኢሕቲላም (በህልም በማየት የሚፈጠር የዘር ፈሳሽ) ሳይሆን (ከባለቤቶቻቸው ጋ በሚፈፅሙት) የግብረ ሥጋ ግንኙነት ምክንያት ጁኑብ ሆነው ፈጅር ይደርስና ቀኑን ይጾሙት ነበር።” (ቡኻሪይ እና ሙስሊም ዘግበውታል።) ሦስተኛው ብይን፦ በአላህ ቤት (ከዕባ) ዙሪያ ጠዋፍ ማድረግ፦ ግዴታ ይሁንም አይሁንም በእርሷ ላይ ክልክል ነው። ተቀባይነትም የለውም። ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ዓኢሻ የወር አበባ ባጋጠማት ጊዜ ተከታዩን ብለዋታልና ነው፦ "ከወር አበባሽ እስክትጠሪ ድረስ ጠዋፍ ከማድረግ ውጪ ሑጃጆች የሚያደርጉትን ሁሉ አድርጊ።" የተቀሩት የሐጅ ተግባራት፦ በአስ-ሰፋ እና አል-መርዋ መካከል መሮጥ፣ ዐረፋ ሜዳ ላይ መቆም፣ በሙዝደሊፋ እና ሚና ላይ ማደር፣ ጀመራት (ጠጠር መወርወር) እና ሌሎች የሐጅ እና የዑምራ ሥርዓቶችን መፈፀም የተከለከሉ አይደሉም። ከዚህም በመነሳት ሴቷ ንፁህ ሆና ጠዋፍ ካደረገች በኋላ ወድያውኑ የወር አበባዋ ቢመጣ ወይም ደግሞ በሰዒይ (በሰፋና መርዋ መካከል በምትሮጥበት) ወቅት ከመጣ ምንም ችግር የለውም። አራተኛው ብያኔ፦ የመሰናበቻ ጠዋፍ (ጠዋፍ አል ወዳዕ) ይቀርላታል። ሴትየዋ የሐጅና የዑምራን ሥርዓት ጨርሳ ወደ ሀገሯ ከመመለሷ በፊት የወር አበባ ካየች እና የወር አበባዋ እስከ መመለሻ ጊዜዋ ድረስ ካላበቃ የመሰናበቻ ጠዋፍ ሳትፈፅም መመለስ ትችላለች። ምክንያቱም ዐብደላህ ኢብኑ ዐባስ (አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸው) ተከታዩን ሐዲሥ አስተላልፈዋልና ነው፦ "ሕዝቡን የመጨረሻ ተግባራቸው በቤቱ (በካዕባ) ዙሪያ ጠዋፍ ማድረግ እንዲሆን አዘዙ፤ በወር አበባ ላይ ላለች ሴት ግን አግራርተዋል።" (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።) በወር አበባ ላይ ያለች ሴት ከሓጅ ስነስርአት የመሰናበቻ ጊዜዋ ሲደርስ ወደ ተከበረው መስጂድ ደጃፍ መጥታ ዱዓ እንድታደርግ አይመከርም። ምክንያቱም ተግባሩ ከነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ተግባር ጋ አልተገኘምና ነው፤ ዒባዳዎች ደግሞ (ከመልዕክተኛው) በተነገሩን (አስተምህሮ) ላይ ብቻ የተመሰረቱ ናቸው። ይልቁኑ እንደውም ከነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) የተነገረው ከዚህ በተቃራኒ ነው። ሶፊያ (ረዲየሏሁ ዓንሀ) ጡዋፈል ኢፋዷ ካደረገች በኃላ የወር አበባዋ መጥቶ ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን)“እንግዲያው ሂጂ።” ብለዋታል። (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።) ወደ መስጂዱ በር እንድትመጣ አይደለም ያዘዟት፤ በሸሪዓ የተደነገገ ቢሆን ኖሮ ደግሞ ባብራሩላት ነበር። የሐጅና የዑምራ ጠዋፍን’ ግን አይቀርላትም፤ ከወር አበባዋ ስትጠራ ጠዋፍ ማድረግ ይጠበቅባታል። አምስተኛው ብይን፦ መስጂድ ውስጥ መቆየት (መቀመጥ)፤ በወር አበባዋ ላይ ላለች ሴት መስጂድ ውስጥ መቆየት የተከለከለ ነው። የዒድ ሰላት ቦታም ቢሆን እመስገጃው ላይ መቆየት የተከለከለ ነው። ማስረጃው የኡሙ ዐጢያህ (አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላት) ያስተላለፈችው ሐዲሥ ነው። የአላህ መልዕክተኛ ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም ተከታዩን ሲናገሩ መስማቷን ገልጻለች፦ "(ለዒድ ሶላት) ልጃገረዶች፣ በጫጉላ ውስጥ ያሉና በወር አበባ ላይ ያሉ ሴቶችም ይውጡ" ካሉ በኋላ፦ "የወር አበባ ላይ ያሉ ሴቶች ግን ከመስገጃ ስፍራው ራቅ ይበሉ።" (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል) ስድተኛው ብይን፦ ግንኙነት፦ ባል ከባለቤቱ ጋ ጾታዊ ግንኙነት መፈጸሙ የተከለከለ ነው። እርሷም ለዚህ ተግባር ፈቃደኛ መሆኗ የተከለከለ ሐራም ነው። አላህ እንዲህ ብሏልና፦ "ከወር አበባም ይጠይቁሃል። እርሱ አስጠያፊ ነው። ሴቶችንም በወር አበባ ጊዜ ራቋቸው። ንጹሕ እስከሚሆኑም ድረስ አትቅረቡዋቸው።" [አን'በቀራ፡ 222] የወር አበባ በሚለው የተፈለገው የወር አበባ ጊዜ እና ቦታ ነው፤ ቦታው የሴት ብልት ነው። በወር አበባ ጊዜ (ተብሎ የተተረጎመው “መሒድ”) በሚለው የተፈለገበት የወር አበባ ጊዜውንም ቦታውንም ነው፤ ቦታው ደግሞ የሴቷ ብልት ነው። ሙስሊሞች የወር አበባ ላይ ካለች ሴት ጋ ግንኙነት መፈፀም የተከለከለ መሆኑን በአንድ ድምፅ የተስማሙበት ጉዳይ ነውና። በመሆኑም በአላህና በመጨረሻው ቀን

ለሚያምን ሰው በአላህ ኪታብ፣ በመልእክተኛው ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሱና እና በመላ ሙስሊሞች ስምምነት የተከለከለውን ይህን የሚያስወቅሰውን ተግባር መፈጸም አይፈቀድለትም። አላህንና መልክተኛውን ከተቃወሙት ከምእመናንም መንገድ ሌላ ከተከተሉትና ካፈነገጡት ጎራ ያደርገዋልና። የአል-ሙሀዘብ ሸርሕ በሆነው አል-መጅሙዕ ገፅ 374 ቅጽ 2 ላይ አሽሻፊዒይ አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ ብለዋል፡- "ይህን የሚያደርግ ሰው ከባድ ወንጀል ሰርቷል።" ጓዶቻችን እና ሌሎችም እንዲህ ብለዋል፦ "በወር አበባ ላይ ካለች ሴት ጋ ግንኙነት ማድረግን የፈቀደ ሰው በከሀዲነት ይፈረድበታል።" የኢማሙ አንነወዊይ ንግግር እዚህ አበቃ። ምስጋና ለአላህ ይሁን! ከግንኙነት ውጪ ባለ መልኩ ፍላጎቱን ማስታገስ የሚችልበትን ያክል ተፈቅዶለታል፤ ሴቷን ቡብልት በኩል ከመገናኘት ውጭ ባሉ እንደ መሳምና መተቃቀፍ እና መተሻሸት ተፈቅዶለታል። ነገር ግን በእምብርቷ እና ጉልበቷ መካከል ያለውን የአካል ክፍሏ ሳይሸፍኑ አለመነካካቱ የተሻለ ነው። ምክንያቱም እናታችን ዓኢሻ (አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላት) እንዲህ ብላለችና፦ "ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) የወር አበባ ላይ እያለሁ ሽርጤን እንድታጠቅ ያዝዙኝ እና ይገናኙኝ ነበር።" (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል) ሰባተኛው ብይን፦ ፍቺ፦ ባል ሚስቱ የወር አበባ ላይ እያለች መፍታቱ ክልክል ነው። አላህ እንዲህ ብሏልና፦ "አንተ ነቢዩ ሆይ! ሴቶችን መፍታት ባሰባችሁ ጊዜ፤ ለዒዳቸው ፍቱዋቸው።" [አጥ'ጠላቅ፡ 1] ማለትም፡- ፍቺው በሚፈፀምበት ጊዜ የታወቀ ዒዳ መቁጠር በሚችሉበት ሁኔታ ይሁን ማለት ነው። ይህ ደግሞ ወይ ነፍሰፁር አልያም ግንኙነት የሌለበት ጡህራ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው። ምክንያቱም በወር አበባ ላይ ሳለች ከተፈታች ይህ የጀመራት ሓይድ ዒዳዋ ላይ አይቆጠርላትም፤ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት በኋላ ከወር አበባዋ ንጹሕ ሆና ከተፈታች ደግሞ የምትቆጥረው ዒዳ ከዚህ ግንኙነት በማርገዟ ምክንያት የነፍሰ ፁርን ዒዳ ነው? ወይስ ከግንኙነቱ ስላላረገዘች የምትቆጥረው ዒዳ የሓይድ ዒዳ ነው? በሚለው ሁኔታ የትኛውን ዒዳ መቁጠር እንዳለባት አያስታውቅም። በዚሁ ሁኔታዋ የትኛውን ዒዳ (ፍቺ እውን ከመሆኑ በፊት አሏህ የወሰነው የመጠባበቂያ ጊዜ) መቁጠር እንዳለባት በርግጠኝነት ማወቅ ስለማይቻል ግልጽ እስኪሆን ድረስ ፍቺ መፈጸመ ክልክል ይሆናል። በመሆኑም በወር አበባ ላይ ያለችን ሴት በወር አበባዋ ሳለች መፋታት ባሳለፍነው አንቀጽ መሰረት የተከለከለ ነው። በቡኻሪና ሙስሊም በሌሎችም የሐዲሥ መዛግብት በተረጋገጠ ሰነድ ኢብኑ ዑመር እንዲህ ማለታቸው ተላልፏል: "ኢብኑ ዑመር ሚስቱን በወር አበባ ላይ እያለች ፈታት፤ እና ዑመርም ረዲየሏሁ ዓንሁ ለነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ነገራቸው፤ የአላህ መልእክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለምም በጉዳዩ ተቆጥተው እንዲህ አሉ፦ "እንዲመልሳትና ከዚያም ንጹሕ እስክትሆን ድረስ እርሱ ዘንድ እንድትቆይ አድርጎ ከዚያም የወር አበባዋ መጥቶ ድጋሚ እስክትጸዳ ድረስ ጠብቆ ከዚያ በኃላ ከፈለገ ይመልሳት ከፈለገም ሳይነካት ይፍታት። ይህ ነው አላህ ሴቶች እንዲፈቱ ያዘዘበት የዒዳ ጊዜው።" አንድ ባል ሚስቱን የወር አበባ ላይ እያለች ከፈታት ኃጢአተኛ ነውና የበላይ ወደ ሆነው አላህ ተጸጽቶ ተመልሶ ሚስቱን በአላህና በመልእክተኛው መመርያ በገጠመ መልኩ ህጋዊ ፍቺ እንዲፈታት ወደቤቱ መመለስ አለበት። ከመለሳትም በኋላ ሲፈታት ከነበራት የወር አበባ ንፁህ እስክትሆን ድረስ ይተዋታል። ከዚያም ድጋሚ የወር አበባ ታያለች ከዚያም ከወር አበባዋ ስትጠራ ከፈለገ ከራሱ ጋር ያቆያት፤ ከፈለገም ደግሞ ከእርሷ ጋ ግንኙነት ሳይፈጽም ይፈታታል። በወር አበባ ጊዜ የሚደረግ ፍቺ ክልክል ነው ሲባል እነዚህን ሶስት ጉዳዮች አይመለከትም፦ አንደኛ፦ ፍቺው የተፈፀመው ከርሷ ጋር አብረው ከማደራቸው ወይም ሳይገናኛት ከሆነ የወር አበባ ላይ እያለች ቢፈታት ምንም ችግር የለበትም። ምክንያቱም በዚያን ጊዜ የምትቆጥረው ዒዳ የላትምና በዚህ ሁኔታ ፍቺ መፈፀሙ ከሸሪዓ አይጋጭም። አላህ እንዲህ ብሏልና፦ "ለዒዳቸው ፍቱዋቸው።" [አጥ'ጠላቅ፡ 1]

ሁለተኛው፦ የወር አበባዋ የመጣው በእርግዝና ወቅት ከሆነ ነው። የዚህን ምክንያት ደግሞ ቀደም ብለን አብራርተናል።

ሦስተኛ፦ ፍቺው ሰውየው ካሳ የሚሰጠው ዓይነት ፍቺ (ኹልዕ) ከሆነ በወር አበባ ላይ እያለች ቢፈታትም ችግር የለውም።

ለምሳሌ በባልና ሚስት መካከል ክርክርና በመጥፎ ሁኔታ እየኖሩ ከሆነ ባልየውም ለመፋታት ካሳ ይወስዳል። ይህ ፍቺ እርሷ የወር አበባ ላይ ብትሆንም ይፈቀዳል። ኢብኑ ዐባስ (ረዲየላሁ ዐንሁ) ሐዲሥ እንዳስተላለፉት የሣቢት ቢን ቀይስ ቢን ሸማስ ሚስት ወደ ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ዘንድ መጣችና፡- “የአላህ መልእክተኛ ሆይ! (ሣቢትን) በሥነ ምግባሩ ወይም በሃይማኖቱ አልወቅሰውም። ነገር ግን በእስልምና ውስጥ ክህደትን እጠላለሁ።” አለቻቸው። ነቢዩም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ አሉ፡- "(ለመሐር የሰጠሽን) የአትክልት ስፍራውን ትመልሽለታሽን?" አሏት። እርሷም፦ “አዎ!” አለች። የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ አሉት፡- "የአትክልት ስፍራህን ተቀበልና አንድ ግዜ ፍታት።" (ቡኻሪይ ዘግበውታል)። ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን)፡- የወር አበባ ላይ ወይም ንፁህ መሆኗን አልጠየቁም። ይህ ፍቺ ለሴቲቱ በራሷ ቤዛ ያደረገችው ስለሆነም በየትኛውም ሁኔታ ይሁን አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ይፈቀዳል። አል-ሙግኒ በተሰኘው ኪታብ ገጽ 52 ምዕራፍ 7 ውስጥ ሴቷ በወር አበባ ላይ ብትሆንም “ኹልዕ” (ሴት ፍቺን መጠየቋ) ለመቻሉ እንደምክንያት ሲያስቀምጡ እንዲህ ብለዋል: "ምክንያቱም በወር አበባ ወቅት ፍቺን የሚከለክለው ዒዳ በምትቆጥርበት (በምትጠብቀው ጊዜ) መራዘም ምክንያት የሚመጣውን ጉዳት ለመከላከል ነው፤ ኹልእ ማለት ደግሞ በመጥፎ የመኗኗር ዘይቤ ምክንያት የሚደርስባትን ጉዳት እና ከምትጠላው እና ከማትወደው ሰው ጋ በመቆየት የሚደርስባትን ጉዳት ለማስወገድ ነው። ይህ ደግሞ ረጅም የጥበቃ ጊዜ ከማሳለፍም የባሰ ጉዳት የሚያስከትል ነው። በዚህም ምክንያት ከሁለቱ የባሰውን በዝቅተኛው መከፈል ተፈቀደ፤ ለዚህም ነው ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ኹልዕ የፈለገችዋን ሴት ስለ ሁኔታዋ ያልጠየቁት።" ንግግራቸው አበቃ።

በወር አበባ ላይ ያለች ሴት የጋብቻ ውልን መፈጸሟን (ኒካሕ ማሠሯን) በተመለከተ ምንም ችግር የለውም። ምክንያቱም በመሠረቱ የተፈቀደ ነውና ለመከልከል የሚያስችል ምንም ማስረጃ የለም። ነገር ግን ባልየው አብሯት መሆኑን በተመለከተ ምልከታ ያሻዋል፤ እንደማይገናኛት የሚታመንበት ከሆነ ምንም ችግር የለውም፤ ያለበለዚያ ግን እርም ነገር ውስጥ መውደቅን ከመጠንቀቅ አኳያ እስክትጸዳ ድረስ እርሱ ቤት ባትገባ ይሻላል።

ስምንተኛ ብያኔ፦ የፍቺ ዒዳን በሱ - ማለትም: በወር አበባ መቁጠር፦ አንድ ሰው ሚስቱን ከተገናኘ በኋላ ወይም ከእርሷ ጋ ብቻውን ተገልሎ ከሆነ ነፍሰ ጡር ካልሆነችና የወር አበባ የምታይ ከሆነ ሦስት ሙሉ የወር አበባ ዑደቶችን መጠበቅ አለባት። አላህ እንዲህ ብሏል፦ "የተፈቱ ሴቶችም ነፍሶቻቸውን (ከማግባት) ሦስትን ቁርእ ይጠብቁ።" [አን'በቀራ፡ 228] “ሦስትን ቁሩእ” ማለት፦ ሦስት የወር አበባ ዑደት ማለት ነው። እርጉዝ ከሆነች የእርግዝና ጊዜዋ ረጅምም ይሁን አጭር የምትጠባበቀው እስክትወልድ ድረስ ነው። አላህ እንዲህ ብሏልና፦ "የእርግዝና ባለቤቶችም ጊዜያቸው እርጉዛቸውን መውለድ ነው።" [አጥ'ጠላቅ፡ 4] እንዲሁም የወር አበባ የሌላት ሴት ከሆነች - ለምሳሌ የወር አበባ ያልጀመረች ታዳጊ ወይም በእርጅና ምክንያት የወር አበባ ማየት ያቆመች ሴት

ወይም ማህፀኗ በቀዶ ጥገና የወጣች ሴት ወይም በሌላ ምክንያት የወር አበባ የሌላት ከሆነች - በወር አበባ ላይ ተመርኩዞ የመመለሻ (ዒዳ ለመቁጠር) ተስፋ ከሌላቸው መካከል ከሆነች የመቆያ ጊዜዋ ሦስት ወር ነው። አላህ እንዲህ ብሏልና፦ "እኒያም ከሴቶቻቸው ከአደፍ ያቋረጡት (በዒዳቸው ሕግ) ብትጠራጠሩ ዒዳቸው ሦስት ወር ነው። እኒያም ገና አደፍን ያላዩት (ዒዳቸው እንደዚሁ ነው)።" [አጥ'ጠላቅ፡ 4] የወር አበባ ከሚያዩ ሴቶች መካከል ብትሆንና ነገር ግን የወር አበባዋ የታወቁ በሆኑ እንደ ህመም እና ጡት ማጥባት ባሉ ምክንያቶች የቀረባት ከሆነ ምንም እንኳን ረጅም ቢወስድባትም የመጠባበቂያ ጊዜዋን (ዒዳ) በወር አበባ እንድትቆጥር የወር አበባዋ እስኪመለስ ድረስ ጠብቃ ዒዳዋን ትቆጥራለች። መንስኤው ተወግዶም የወር አበባዋ ካልተመለሰ ደግሞ ማለትም ከበሽታው ከዳነች ወይም ጡት ማጥባት ካቆመች ነገር ግን የወር አበባዋ ድጋሚ ካልመጣ መንስኤው መጥፋቱ ከተረጋገጠበት ጀምሮ ለአንድ ዓመት ያህል ዒዳዋን ትቆጥራለች። የሸሪዓ መርሆችን የሚገጥመው ትክክለኛው አባባል ይህ ነው። መንስኤው ተወግዶም የወር አበባዋ ካልተመለሰ ባልታወቀ ምክንያት የወር አበባዋ እንደቀረባት ሴት ትቆጠራለች። ባልታወቀ ምክንያት የወርአበባዋ የቀረባት ሴት ደግሞ ምናልባት እርግዝና ሊሆን ስለሚችል ለአንድ ዓመት ያህል ዒዳ ትቆጥራለች፤ ምክንያቱም በአብዛኛው የእርግዝና ወቅት ዘጠኝ ወር ስለሆነ እና ሦስቱ ወር ደግሞ ለዒዳ ነው። ነገር ግን ፍቺው ከውል በኋላ እና ግንኙነትም ሳይደርጉና ለብቻቸውም ሳይገለሉ በፊት ከሆነ የወር አበባም ሆነ ሌላ ምንም የመጠባበቂያ ጊዜ አይኖርም። አላህ እንዲህ ብሏልና፦ "እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ምእምናትን ባገባችሁና ከዚያም ሳትነኩዋቸው በፊት በፈታችኋቸው ጊዜ ለእናንተ በእነርሱ ላይ የምትቆጥሩዋት ዒዳ ምንም የላችሁም።" [አን'አሕዛብ፡ 49]

ዘጠነኛ ብይን፦ የማህፀን ከፅንስ ነፃ መሆን። ማለትም ከእርግዝና ነፃ መሆኗ ማለት ነው። አንዲት እንስት ከእርግዝና ነፃ መሆኗ መታወቁ ተያያዥ ህግጋትን በተግባር ለማዋል ስለሚረዳ የማህፀኗ ነፃ መሆን ለተለያዩ ጉዳዮች ምላሽ ይሰጣል።

ከእነዚህም መካከል ለምሳሌ፦ የአንዲት ሴት ባል ቢሞትና (እርሷ ሌላ ሰው ብታገባ) ከአዲሱ ባሏ ጋር ግብረስጋ ከመፈፀሟ በፊት ማህፀኗ ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ የወር አበባዋ መጥቶባት ፈስሶ እስኪያበቃ መጠበቃቸው ወይም እርግዝናዋ በግልፅ መኖሩን ማረጋገጥ የግድ ነው። ምክንያቱም በማህፀኗ ከሟች የተረገዘ ፅንስ ካለ ሟች አባቱ በህይወት ሳለ የተፈጠረ ነውና እሱን የሚወርስ መሆኑ ውሳኔ ይሰጥበታል። ከባሏ ሞት በኋላ የወር አበባ ካየች ግን ማህፀኗ ከፅንስ ነፃ መሆኑን ስለሚያመለክት ከዚህ በኋላ የምታረግዘው ልጅ ሟችን የማይወርስ ለመሆኑ ብያኔ ይሰጥበታል።

አስረኛው ብይን: መታጠብ ግዴታ ስለመሆኑ። በወር አበባ ላይ ያለች ሴት ንፁህ ስትሆን ሰውነቷን በሙሉ መታጠብ አለባት። ምክንያቱም ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ለፋጢማህ ቢንት አቢ ሑበይሽ እንዲህ ብለዋታልና፦ “የወር አበባሽ ሲመጣ ሶላት ከመስገድ ታቀቢ፤ ሲያበቃ ደግሞ ታጠቢና ስገጂ።” (ቡኻሪይ ዘግበውታል።) በጣም ትንሹ የግዴታ ትጥበት ሁሉንም የሰውነቷን ክፍል ከፀጉሯ ስር ያለውንም (የራስ ቅሏን) ጨምሮ አዳርሶ ማጠብ ነው። በሐዲሥ ላይ በተጠቀሰው አኳኃን መታጠቧ ደግሞ በላጭና ተመራጭ ነው። ነቢዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) አስማእ ቢንት ሺክል የወር አበባን ትጥበት በተመለከተ ስትጠይቃቸው የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋታል፦ "ከእናንተ መካከል አንዷ (መታጠብ ስትፈልግ) ውሃውንና የቁርቁራ ዛፍ ቅጠል (መልካም መዓዛ ያለው እንደ ሳሙና የሚያገለግል ቅጠል) ተጠቅማ አሳምራ ትታጠብ። ከዚያም አናቷ ላይ ውኋ ታፍስስና ውኋው ወደራስ ቅሏ እስኪዘልቅ ድረስ ፍትግ አድርጋ ትሸው። አሁንም በድጋሚ በአናቷ ላይ ውሃ ታፈስሳለች። ከዚያም ሚስክ (መልካም ሽታ ያለው የሽቶ ዘር) የተቀባበት ጨርቅ ትወስድና በሱ ታፀዳበታለች።» አሏት። የዚህን ግዜ አስማእ "እንዴት ነው የምታፀዳበት?" ስትል ጠየቀቻቸው። እርሳቸውም "ሱብሓን አላህ!" አሉ። የዚህን ግዜ እናታችን ዓኢሻ (ረዲየላሁ ዐንሃ) “የደሙን ፋና እየተከተልሽ ታፀጂበታለሽ።” ስትል መለሰችላት። [ሙስሊም ዘግበውታል] በዚህ ትጥበት ወቅት ፀጉሯ በጥብቅ የተቆጣጠረ ወይም የተሰራም ሆኖ ውሃው ፀጉሯ ስር የራስ ቅሏ ድረስ ላይደርስ ይችላል ተብሎ ካልተፈራ በስተቀር ፀጉሯን መፍታት ግዴታ አይሆንባትም። የዚህም ማስረጃ ሙስሊም እንደዘገቡትና በኡሙ ሰለማ (ረዲየላሁ ዐንሃ) ሐዲሥ እንደተወሳው የአላህ መልእክተኛን (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) “እኔ ፀጉሬን የምቋጥር ሴት ነኝና ለጀናባ ትጥበት ስል መፍታት ይጠበቅብኛልን?” በሌላ ዘገባ ደግሞ፦ “ለሐይድ እና ለጀናባ ትጥበት ስል መፍታት ይጠበቅብኛልን?” ስትል ጠየቀቻቸው። እርሳቸውም፦ “አይ አይጠበቅብሽም። በአናትሽ ላይ ሶስቴ ውኋ ካፈሰስሽ በኃላ በሰውነትሽ ላይ እያዳረስሽ መተጣጠብ ብቻ ነው የሚጠበቅብሽ።” አሏት።

አንዲት ሴት በሰላት ወቅት ከወር አበባዋ ከጠራች ሰላቷን በወቅቱ እንድትሰግድ ቶሎ ብላ ገላዋን መታጠብ ግዴታ ይሆንባታል። መንገደኛ ከሆነችና ውሃ ካጣች ወይም ውሃ ቢኖራት እንኳ በዚህ ውሃ ከታጠብኩበት መንገደኛ ነኝና ውሃዬን ጨርሼው ልቸገር እችላለሁ ብላ ከፈራች ወይም በውሃ መታጠቧ የሚጎዳት ህመምተኛ ከሆነች በውሃ እንዳትታጠብ ከልካይ የሆነው ችግሯ እስኪወገድ ድረስ በትጥበቱ ፋንታ ተየሙም ታደርጋለች። ከዚያም ችግሯ በተወገደ ግዜ በውሃ ትጥበቷን ትፈፅማለች።

አንዳንድ ሴቶች በሰላት ወቅት ከወር አበባቸው ይፀዳሉ። ነገር ግን የተሟላ የሆነ አስተጣጠብን ለመታጠብ ግዜው አይበቃኝም በሚል ሰላቱን ያዘገዩታል። ይሁንና ይህ ሰላትን ለማዘግየት መረጃም በቂ ምክንያትም ሊሆናቸው ፈፅሞ አይችልም። ምክንያቱም ግዴታ የሚሆንባትን አስተጣጠብ ብቻ ቶሎ ታጥባ ሰላቷን በወቅቱ መፈፀምና ከዚያም በቂ ግዜ ስታገኝ የተሟላ የሆነውን አስተጣጠብ መታጠብ ትችላለችና።

*

# ክፍል አምስት፡ ኢስቲሓዷን የተመለከቱ ሕግጋት

ኢስቲሓዷህ ማለት ፦ በሴቷ ላይ የሚከሰት ዘውታሪነት ያለው ደም ሲሆን፤ ያለማቋረጥ የሚፈስ ወይም ደግሞ ለአጭር ጊዜ ብቻ ለምሳሌ በወር ውስጥ ለአንድ ወይም ለሁለት ቀናት ብቻ የሚቋረጥ የደም ፍሰት ነው።

ለመጀመሪያው አይነት ምሳሌ ማለትም ደሙ ፍፁም ለማይቋረጥበት ሁኔታ ማስረጃው እናታችን ዓኢሻ (አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላት) እንደተናገረችውና በተረጋገጠ ሰነድ በሰሒሕ አል ቡኻሪ እንደተዘገበው እንዲህ ማለቷ ነው፦ “ፋጢማ ቢንት አቢ ሑበይሽ ለአላህ መልእክተኛ ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም እንዲህ አለቻቸው፦ ‘የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኔ (ከወር አበባ) ንፁህ አልሆንም።’ በሌላ ዘገባ ደግሞ፦ ‘የወር አበባ አያለሁ ግን አልጠራም።’” ለሁለተኛው አይነት ሁኔታ ማለትም ደሙ ለትንሽ ጊዜ ካልሆነ በቀር ለማይቋረጥበት ለሆነ ሰው ማስረጃው የሐምና ቢንት ጀሕሽ ሐዲስ ነው። ወደ ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ዘንድ መጥታ እንዲህ አለች፦ "የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኔ የወር አበባ እጅግ በጣም ብዙ ጊዜ እያየሁኝ ነው።"

[ሐዲሡን አሕመድ፣ አቡ ዳውድና ቲርሚዚይ ዘግበውታል። ቲርሚዚይ ሶሒሕ ብለውት ኢማሙ አሕመድ ሶሒሕ ቡኻሪይ ደግሞ ሓሰን ማለታቸውንም ጠቅሰዋል።]

የኢስቲሓዷ ሁኔታዎች፦

ኢስቲሓዷህ ያለባት ሴት ሦስት ዓይነት ሁኔታዎች ይኖራታል፦

የመጀመሪያው ሁኔታ ፦ ገና ኢስቲሓዷ ሳያጋጥማት በፊት የታወቀ የወር አበባ ወቅት የነበራት። የዚህች ዓይነቷ ሴት ቀደም ሲል የነበራትን የወር አበባ ልምዷን መመዘኛ ታደርጋለች። (በወር አበባ ጊዜ የምትከለከላቸውን ነገሮች ሁሉ እንደ ሶላት እና ፆም ያሉ ተግባራት) ትታቀባለች የወር አበባን የተመለከቱ ብይኖችም ተፈፃሚ ይሆንባታል። ከነዚህ የልምድ ቀናቶቿ ውጪ ያሉ ቀናት የኢስቲሓዷህ ደም ቀናት ይባላሉ። የኢስቲሓዷ ብይንም ተፈፃሚ ይሆንባታል።

የዚህም ምሳሌው ሴቷ ከየወሩ መጀመርያ ባሉ ጊዜያት ለስድስት ቀናት የወር አበባ የምታይ ብትሆንና ከዚያም የኢስቲሓዷ ደም ተከስቶባት ደም ያለማቋረጥ ቢመጣባት፤ የወር አበባዋ በየወሩ መጀመሪያ ላይ ያሉት ስድስት ቀን ይሆናል፤ ከነዚህ ውጪ ያሉ ቀናት ደግሞ ኢስቲሓዷ ይሆናል። ማስረጃውም እናታችን ዓኢሻ ባስተላለፉችው ሐዲሥ ፋጢማ ቢንት አቢ ሑበይሽ (መጥታ)፦ "የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኔ ያለማቋረጥ ደም ይፈስብኛል። የንፅህና ጊዜ ሊኖረኝ አልቻለም። ሶላቱን ልተውን?" አለቻቸው። እርሳቸውም ፦ "አይደለም! ይህ ከደም ቧንቧ የሚፈስ ነው። ይሁን እንጂ ቀደም ሲል የወር አበባ ስታይ በነበርሽባቸው ቀናት ልክ ሶላትሽን ተይ! ከዚያም ታጠቢና ስገጂ።" አሏት። (አልቡኻሪይ ዘግበውታል።) በሰሒሕ ሙስሊም ላይ ደግሞ፦ ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ለኡሙ ሐቢባ ቢንት ጀሕሽ እንዲህ ብለዋታል፦ "(ከዚህ ቀደም) የወር አበባሽ እስከሚያቅብሽ ቀናት ድረስ ታቀቢ ከዚያም ታጠቢና ስገጂ።" ከዚህም በመነሳት የወር አበባ ቀናቷ የታወቀች ሴት የወር አበባዋ በሚቆይበት ጊዜ ልክ ትታቀብና ከዚያም ታጥባ ሰላቷን ትሰግዳለች። ከዚያ በኃላ ለሚመጣው ደም መጨነቅ የለባትም።

ሁለተኛው ሁኔታ፦ ከኢስቲሓዷዋ በፊት የታወቀ የወር አበባ ወቅት ያልነበራት እና ኢስቲሓዷው የጀመራት ገና ደሟን እና ኢስቲሓዷውን ለይታ ሳታውቅ ደም ካየችበት ጊዜ ጀምሮ ዘውታሪነት ባለው መልኩ ከሆነ ደሟን በምልክት እንድትለይ ትደረጋለች። በዚህም መሰረት የሐይድ ደም ጥቁረት፣ ውፍረት እና ሽታ ያለው ሲሆን (የዚህ አይነቱ ደም) የወር አበባ ብይኖች የሚመለከተው ደም ነው። ከዚህ ውጪ ያለው የደም አይነት ደግሞ እንደ ኢስቲሓዷ ይቆጠርና የኢስቲሓዷ ብይኖች የሚፀናበት ይሆናል።

በምሳሌ ስንመለከተው፦ አንዲት ሴት የማያቋርጥ የደም ፍሰት ታየለች። ነገር ግን በመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት የሚፈሰው ደም ጥቁር ሲሆን በተቀሩት የወሩ ቀናት እየፈሰሳት ያለው ደም ደግሞ ቀይ ነው። ወይም ደግሞ በመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ወፍራም ደም እያየች ቆይታ በቀሪው የወር ቀናት ቀጭን ደም ታያለች። ወይም በመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት የሐይድ ደም ሽታ ያለው ይሆንና በተቀሩት የወሩ ቀናት የሓይድ ደም ሽታ የሌለው ይሆናል። (በዚህም መሰረት) የወር አበባ ጊዜዋ በመጀመሪያው ምሳሌ ጥቁሩ፣ በሁለተኛው ምሳሌ ወፍራሙ፣ በሦስተኛው ምሳሌ ደግሞ ሽታ ያለው ይሆናል። ከዚህ በኋላ ያለው የደም መፍሰስ እንደ ኢስቲሓዷህ ይቆጠራል። ምክንያቱም ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ለፋጢማህ ቢንት አቢ ሑበይሽ እንዲህ ብለዋታልና ነው፦ "የወር አበባ ደም ሲመጣ ጠቆር ብሎ ሊታወቅ የሚችል ነው፤ ይህ በመጣ ጊዜ ከሶላት ተቆጠቢ፤ ሌላ አይነት ደም ከሆነ ግን የደም ስር መበጠስ ነውና ውዱእ አድርገሽ ስገጂ።" [አቡ ዳውድና ነሳኢይ ዘግበውት ኢብኑ ሒባንና አልሓኪምም ሶሒሕ ብለውታል።] ምንም እንኳን ይህ ሐዲሥ በዘገባ ሰንሰለቱም (ሰነዱ) ይሁን መትኑ (የቃላት አወቃቀሩ) ምልከታ የሚሻ ቢሆንም ዑለሞች (አላህ ይዘንላቸውና) ተግባራዊ ያደረጉት ነው። አብዛኛዎቹ ሴቶች የሚያጋጥማቸውን አማካይ የወር አበባ ጊዜ (ስድስት ወይም ሰባት ቀናት) ከማመሳከር ይልቅ (በመለያ ምልክቶቹ መለየቱ) የተሻለ ማመሳከሪያ ነው። ሦስተኛው ሁኔታ፦ ሴትየዋ የሚፈሳት ደም የታወቀ የወር አበባ ዑደት ወቅት እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት መለያ ባህሪያትም አላገኘችለትም! የደም ፍሰቱም ቀጣይነት ያለውና ተመሳሳይ ባህሪ ወይም ያልተለመዱ ባህሪያትን ይዞ የሚፈስ ሲሆን የወር አበባ ደም ነው ለማለትም አስቸጋሪ የሆነ ነው። የዚህ ዓይነት ሁኔታ የገጠማት ሴት የአብዛኛዎቹ ሴቶች ልማድ በመውሰድ የወር አበባ ደም ካየችበት የመጀመሪያ ጊዜ ጀምሮ በየወሩ ስድስት ወይም ሰባት ቀን የወር አበባ ጊዜዋ አድርጋ ትቆጥራለች። የተቀሩት ቀናት የኢስቲሓዷህ ይሆናሉ ማለት ነው። የዚህ ምሳሌውም፦ አንዲት ሴት በወሩ አምስተኛው ቀን ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የደም ፍሰት ያጋጥማታል፤ ከዚያም በቀለምም ይሁን በሌላ ነገር የወር አበባ መሆኑን መለየት አልቻለችም። ይህኔ የወር አበባ ጊዜዋ በየወሩ ስድስት ወይም ሰባት ቀናት ይሆናል። በየወሩ ከአምስተኛው ቀን ጀምሮም የወር አበባዋን የምትቆጥርበት ጊዜ ይሆናል። ሐምና ቢንት ጀሐሽ ባስተላለፉችው ሐዲሥ እንዲህ የሚል አለና፦ "አንቱ የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ትልቅ እና ከባድ የወር አበባ እያጋጠመኝ ነው፤ ሶላትም ፆምም ማከናወን አልቻልኩምና በዚህ ጉዳይ ምን ይሉኛል?" አለቻቸው። የአላህ መልዕክተኛም (ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም)፦ "እኔ የምገልፅልሽ ጥጥ እንድትጠቀሚ ነው፤ ደሙን ስለሚመጠው ማህፀንሽ ላይ አድርጊው ብየ ነው።" አሏት እርሷም፦ "ከዚህም በላይ ነው።" አለቻቸው። በዚህ ሐዲሥ ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብለዋታል፦ "ይህ ከሰይጣን እርግጫዎች አንዱ ነውና የትኛው መሆን እንዳለበት አላህ በሚያውቀው (የተሻለ ሚዛናዊ የሆነውን ከቤተሰቦችሽ ልማድ አንፃር አይተሽ) በወር አበባሽ ለስድስት ወይም ለሰባት ቀናት ታቀቢ። ከዚያም ታጥበሽ ንጹሕ መሆናሽን ካመንሽበት ጊዜ በኃላ የተቀሩትን ሀያ ሦስት ወይም ሀያ አራት ቀንና ሌሊት ስገጂም ፁሚም።" ሐዲሡን [አሕመድ፣ አቡ ዳውድና ቲርሚዚይ ዘግበውታል። ቲርሚዚይ ሶሒሕ ብለውት ኢማሙ አሕመድ ሶሒሕ ቡኻሪይ ደግሞ ሓሰን ማለታቸውንም ጠቅሰዋል።] የአላህ መልዕክተኛ "ስድስት ወይም ሰባት ቀን" ሲሉ (ለሐምና ቢንት ጀሕሽ) ምርጫን ለመስጠት ሳይሆን ለእርሷ (ከሌሎች ሴቶች መካከል) በእድሜ፣ በሰውነት አወቃቀሯ፣ በልጆች ቁጥር ብዛት ማን እንደሚቀርባት እንዲሁም ከደም አኳያ ለወር አበባዋ ይበልጥ ቅርብ የሆነውን እና ሌሎችንም ጉዳዮች በተመለከተ እንድትመረምር እና እንድታጣራ ነው። ከአምሳዮቿ አንፃር ለርሷ ይበልጥ ቅርብ የሆነው ለስድስት ቀናት ከሆነ ስድስት ታደርገዋለች። ለርሷ ይበልጥ ቅርብ የሆነው ለሰባት ቀናት ከሆነ ደግሞ ሰባት ታደርገዋለች።

ከኢስቲሓዷህ ጋር የሚመሳሰሉ ሁኔታዎች፦

አንዲት ሴት ከብልቷ ደም እንዲፈስ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ በማህፀን ላይ በሚደረግ ቀዶ ጥገና ወይም በሌላ ምክንያት ሊከሰት ይችላል። ይህም ሁለት ዓይነቶች አለው፦

የመጀመሪያው ዓይነት፦ ከቀዶ ጥገናው በኋላ የወር አበባ ማየት እንደማትችል የሚታወቅ ከሆነ ለምሳሌ ቀዶ ጥገናው ማህፀኗን ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ ወይም ደም እንዳይወጣ ለመዝጋት ከሆነ የዚህች ዓይነቷ ሴት የኢስቲሓዷ ብይን ተፈፃሚ አይሆንላትም።

ይልቁንም ብይኗ የወር አበባ ከማይመጣቸው ይልቁን ቢጫ ወይም ቡናማ እርጥበታማነት የሚመለከቱ ሴቶችን ፍርድ ነው ተፈፃሚ የሚሆንባት። በመሆኑም ሶላትን ወይም ፆምን መተው የለባትም ባሏም ከእርሷ ጋር ግንኙነት ማድረግ አይከለከልም። ይህንንም ደም መታጠብ ግዴታ አይሆንባትም። ልትሰግድ ስትል ግን ደሙን መታጠብ አለባት። ብልቷ ላይ ጨርቃ እና መሰል ነገሮች በመጠቀም የሚፈሰውን ደም ለመከላከል መሞከር፤ ከዚያም ለሶላት ውዱእ ማድረግ፤ እንደ አምስቱ ወቅት ሶላቶች አይነት የተገደበ ጊዜ ያለውን ሶላት ልትሰግድ ከሆነ የሶላቱ ወቅት ከመግባቱ በፊት አይደለም ውዱእ የምታደርገው። በጊዜ ያልተገደቡ የሱና ሶላቶችን ልትሰግድ ከሆነ ግን በየትኛውም ሰዓት ልትሰግድ ስትል ዉዱእ ታድርግ።

ሁለተኛው ዓይነት፦ ከቀዶ ጥገናው በኋላ የወር አበባዋ መቆሙ ተለይቶ ያልታወቀና ምናልባት የወር አበባ የማየት እድል የሚኖራት ሲሆን የዚህች ዓይነቷ ሴት የሚሰጣት ብይን የኢስቲሓዷ ደም ብይን ነው። ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ለፋጢማ ቢንት አቢ ሑበይሽ የተናገሩት ነገር የሚየመለክተውም ይህንኑ ነው። "ይልቁን ይህ የወር አበባ ሳይሆን የደም ስር መበጠስ ነውና የወር አበባሽ ሲመጣ ከሶላት ታቀቢ።" "የወር አበባሽ ሲመጣ" የሚለው የረሱል ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም ንግግር የኢስቲሓዷህ ብይን የሚመለከተው የወር አበባዋ ብቅ እልም እያለ ለሚያስቸግራት ነው እንጂ የወር አበባ የሌላትና ወይም የጠፋ መሆኑ ከታወቀማ በማንኛውም ሁኔታ ላይ ደሙ የደም ስር መበጠስ ነው።

የኢስቲሓዷህ ብያኔዎች፦

ከላይ በተመለከትነው መሰረት ደሙ የወር አበባ ደም የሚሆነው መቼ እንደሆነና የኢስቲሓዷህ ደም የሚሆነውም መቼ እንደሆነ አውቀናል። በዚህም መሰረት የወር አበባ ደም በሚመጣበት ጊዜ የወር አበባ ብይኖች ተፈፃሚ ይሆኑበታል። ኢስቲሓዷህ ሲሆን ደግሞ የኢስቲሓዷህ ብይኖች ተፈፃሚ ይሆኑበታል ማለት ነው።

የወር አበባን የተመለከቱ አስፈላጊ የሆኑ ድንጋጌዎችን ቀደም ብለው ተጠቅሰዋል።

ኢስቲሓዷህን የተመለከቱት ብይኖች ልክ ንፁህ በምትሆንበት ጊዜ እንደሚኖራት አይነት ብይኖች ነው። በሚከተሉት ሁኔታዎች ካልሆነ በቀር ኢስቲሓዷህ ባለባት ሴት እና ከወር አበባ ንፁህ በሆነች ሴት መካከል ልዩነት የለም፦

የመጀመርያው፦ ለእያንዳንዱ ሶላት ዉዱእ ማድረግ ግዴታ ይሆንባታል። ምክንያቱም ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ለፋጢማህ ቢንት አቢ ሑበይሽ እንዲህ ብለዋታልና ነው፦ "ከዚያም ለእያንዳንዱ ሶላት ዉዱእ አድርጊ።" (ቡኻሪይ ዘግበውታል፤ በኪታባቸው ገስሉ ደም በሚለው ምዕራፍ ስር አስፍረውታልም።) ይህም ማለት በጊዜ የተገደቡ ሶላቶችን ለመስገድ ከሆነ ወቅታቸው እስኪገባ ድረስ ዉዱእ አታደርግም ማለት ነው። ነገር ግን ሶላቱ በጊዜ ያልተገደበ ከሆነ ሶላቱን መስገድ በምትፈልግበት ጊዜ ዉዱእ ታደርጋለች። ሁለተኛ፦ ዉዱእ ማድረግ ከፈለገች የደሙን ቅሪት ታጥበዋለች። የሚፈሰውን ደም እንዲመጠው ከጥጥ የተሰራ ጨርቅ ብልቷ ላይ ታኖራለች። ምክንያቱ ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ለሐምና እንዲህ ብለዋታል፦ "ደሙን ስለሚመጠው ጥጥ እንድትጠቀሚ እመክርሻለሁ።" ባሏት ጊዜ እርሷም፦ "ከዚህ በጣም ያለፈ ነው" ብላ መለሰች። እርሳቸውም፦ "ልብስ አድርጊበት" አሏት። እርሷም፦ "ከዚህ በጣም ያለፈ ነው" አለች። እርሳቸውም፦ "እንግዲያውስ (ከወገብሽ ጋር አስረሽ) አፍኚው።" አሏት። ከዚያ ሁሉ በኋላ አልፎ የሚወጣው ደም ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ለፋጢማህ ቢንት አቢ ሑበይሽ በነገሯት መሰረት ችግር አይኖረውም። "በወር አበባሽ ቀናት ሶላት ከመስገድ ተቆጠቢ፤ ከዚያም ታጠቢ፤ ለእያንዳንዱ ሶላትም ዉዱእ አድርጊ፤ ከዚያም ደሙ ምንጣፉ ላይ ቢንጠባጠብም እንኳ ስገጂ።" (አሕመድ እና ኢብኑ ማጃህ ዘግበውታል) ሦስተኛ፦ ግብረስጋ ግንኙነት። ካልተገናኘ ዝሙት ላይ እንዳይወድቅ ለማይሰጋ ሰው መፈቀድ አለመፈቀዱን በተመለከተ ዑለሞች በሀሳብ ተለያይተዋል። ትክክለኛው አስተያየት ይፈቀዳል የሚለው ነው። ምክንያቱም በነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ጊዜ ብዙ ሴቶች አስር እና ከዚያም በላይ የሚደርሱ እንስቶች ኢስቲሓዷ ነበረባቸው። አላህም መልእክተኛውም (ባለትዳሮች) የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳይፈጽሙ አልከለከሉም ነበር። እንደውም የበላይ የሆነው አላህ እንዲህ በሚለው ቃሉ፦ "ሴቶችንም በወር አበባ ጊዜ ራቋቸው።" (አል በቀራህ: 222) የጠቆመን ከወር አበባ ውጪ ባለ ማንኛውም አይነት ምክንያት ሴቶችን ከመገናኘት የሚከለክል ምክንያት አለመሆኑን ነው። ሶላትም እንድትሰግድ የተፈቀደላት ከሆነ ግንኙነት ደግሞ ከእርሱ ያነሰና ቀላል ነው። ከእርሷ ጋ ግንኙነት መፈፀም የወር አበባ ላይ ካሉ ሴቶች ጋር ግንኙነት ከመፈፀም አኳያ አንፃራዊ አድርጎ መመልከት ስህተት ነው። ምክንያቱም እንዚህ ሁለቱ ነገሮች፤ ግንኙነት የተከለከለ ነው የሚሉት ዘንድ እንኳ ቢሆን ተመሳሳይ እንዳልሆኑ ግልፅ ነው። በሁለት የተለያዩ ነገሮች መካከል ደግሞ ቂያስ አይደረግም።

*

# ምዕራፍ ስድስት፦ ስለ ወሊድ ደም እና ሕግጋቶቹ

የወሊድ ደም: በወሊድ ምክንያት ከማህፀን ውስጥ የሚፈስ ደም ነው። በወሊድ ጊዜ፣ ከወሊድ በኋላ (ድህረ-ወሊድ) ወይም ከወሊድ በፊት በሁለት ወይም በሶስት ቀናት ልዩነት ስቃይ ታክሎበት የሚከሰት ነው።

ሸይኹል-ኢስላም ኢብን ተይሚያህ እንዲህ ብለዋል፦ “ሴቷ ምጥ ስትጀምር የምታየው የወሊድ ደም ነው።” በሁለት ወይም በሦስት ቀናት ብቻ አልገደቡትም። ማለት የፈለጉት፦ ስቃዩን ተከትሎ የሚመጣ መውለድ ካለ ነው እንጂ ካልሆነ ስለፈሰሰ ብቻ የወሊድ ደም ነው ማለት አይደለም። የቆይታ ጊዜ ገደቡ ቢያንስ ወይም ቢበዛ የሚባል ወሰን አለውን? የሚለውን አስመልክቶ ዑለሞች ተለያይተዋል። ሸይኹል ኢስላም ተቂዩዱዲን (ኢብኑ ተይሚያህ) አሏህ ብይን ያቀራኙባቸውን ስያሜዎችን በተመለከተ በፃፉት ሪሳላቸው (ገጽ 37) ላይ እንዲህ ብለዋል፦ “የወሊድ ደም ቢያንሰ ወይም ቢበዛ ተብሎ የሚቀመጥለት ገደብ የለውም። ለምሳሌ አንዲት ሴት (ከወለደች በኃላ) ከአርባ፣ ከስልሳ ወይም ከሰባ ቀናት በላይ ደም እየፈሰሳት ቆይቶ የደም መፍሰሱ ከዛ በኃላ ቢያቆም የወሊድ ደም ነው። ነገር ግን ደሙ (ሌላ እንደኢስቲሓዷ ዓይነት ደም ከተቀላቀለበት) የተበላሸ ደም ይባላል። እናም በዚህን ጊዜ ገደቡ አርባ ይሆናል። ምክንያቱም በአብዛኛዎቹ ሴቶች የሚያጋጥመው የተለመደው አርባ ቀን በመሆኑ ነው።” (ንግግራቸው አበቃ) እንዲህ አልኩ፦ በዚህም መሰረት የወሊዱ ደም መፍሰስ ከአርባ ቀናት በላይ ከቀጠለ እና በልምዷ ደግሞ ከዚያ በኋላ የደም ፍሰቱ የሚቋረጥበት ጊዜ ከሆነ ወይም እንደሚቆም የሚጠቁሙ ምልክቶችን ማየት ከጀመረች ደሙ መፍሰስ እስከሚቆም መጠባበቅ አለባት። ከነዚህ ምልክቶች መካከል አንዳቸውንም ካላየች ግን አርባ ቀን ሲሞላት ራሷን ታጸዳለች (ትተጣጠባለች)። ምክንያቱም ለወር አበባዋ ስትል ትቀጥል ዘንድ የወር አበባዋ አብሮ ካልመጣ በቀር የብዙዎቹ ልማዳቸው እስከአርባ ቀን ስለሆነ ነው። መደበኛ

የወር አበባዋ ቀናቷ ካለቀ በኋላም ደሙ መፍሰሱን ከቀጠለ ኢስቲሓዷ ስላጋጠማት ቀደም ብለን ያብራራነውን የኢስቲሓዷ ህግጋት ተግባራዊ ታድርግ። አል-ሙቅኒ በተሰኘው ኪታብ እንዲህ ብለዋል: ምናልባት የደም ፍሰቱ የተቋረጠው ከአንድ ቀን በታች ለሆነ ጊዜ ካልሆነ በቀር አርባ ቀንም ሳይሞላት ገና የወሊድ ደም መፍሰሱን (ከአንድ ቀን በላይ ለሆኑ ጊዜያት)ካቋረጠ ሴቷ ንፁህ ስለሆነች ከዚያም ገላዋን ታጥባ መስገድ፣ መጾም እና ከባልዋ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም ትችላለች።
ሴቲቱ ግልጽ የሆኑ የሰው ባህሪያት ያለውን ልጅ ካልወለደች በቀር የወሊድ ደም እንደፈሰሳት አይፀናም። የሰው ልጅ ባህሪ የማይታይበት ትንሽ የፅንስ መጨንገፍ ስለወጣት ብቻ ደሟ የድህረ ወሊድ ደም ነው ሊባል አይችልም። ይልቁኑ ከደም ስር የመጣ (የጅማት) ደም ነው። የሚሰጣት ብይንም የኢስቲሓዷህ ብይን ይሆናል። የሰው ልጅ (በሽሉ ውስጥ) መፈጠሩ የሚታወቅበት ዝቅተኛ ጊዜ እርግዝናው ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ሰማንያ ቀናት ከሞላበት ጊዜ በኃላ ነው፤ አብዛኛው ደግሞ ዘጠና ቀናት ነው።
አልሙጂድ ኢብን ተይሚያህ እንዲህ ብለዋል፦ "(ከ80/90 ቀናት) በፊት ደም ከህመም ጋ ተጣምሮ ካየች ምንም አይነት ግምት ውስጥ ማስገባት የለባትም (ማለትም ሰላትና ፆም ትቀጥላለች) ነገር ግን ከዚህ ወር በኋላ ደም ካየች ከሰላት እና ከመፆም መቆጠብ አለባት። ሁኔታው ከሚታየው ሁኔታ ጋር የሚቃረን ከሆነና በኋላ ጉዳዩ ግልጽ ከሆነ ተመልሳ ማስተካከል አለባት ፤ ጉዳዩ ግልጽ ካልሆነ ግን ግልጽ የሆነው ውሳኔ ይቀጥላል ምንም የሚደገም ነገር አይኖርም።" (ሸርሕ አልኢቅናዕ ላይ አስፍረውታል)
ኒፋስን (የወሊድ ደም) የተመለከቱ ህግጋት፦
የድህረ ወሊድ ደም ብያኔዎች በወር አበባ ላይ ከተሰጡት ብያኔዎች ጋ በሚከተሉት ሁኔታዎች ካልሆነ በቀር ተመሳሳይ ናቸው፦
የመጀመሪያው: ዒዳ (ለፍቺ ሲባል የተወሰነ የመጠባበቂያ ጊዜ) ከወሊድ ደም ጋር ሳይቆራኝ እንደ ፍቺ ይቆጠራል። ምክንያቱም ፍቺው ፅንሱ ከመወለዱ በፊት የተፈፀመ ከሆነ የመቆያ ጊዜው የሚያበቃው በመወለዱ እንጂ በወሊድ ጊዜ አይደለም። ፍቺው የተፈፀመው ከወለደች በኋላ ከሆነ ደግሞ ልክ እንደመጀመሪያው የወር አበባ ድጋሚ እስኪመጣ ድረስ ትጠብቃለችና።
ሁለተኛ: "አልኢላእ" ከእሷ አንፃር የሚሰላው በወር አበባ ጊዜ እንጂ የድህረ ወሊድ ጊዜ መሰረት ተደርጎ አይደለም።
"አል-ኢላእ" ማለት፦ አንድ ሰው ከሚስቱ ጋ ፈጽሞ ወይም ከአራት ወር በላይ ላለ ጊዜ ግንኙነት ላለማድረግ መማሉ ነው። ቢምልና ግንኙነት እንዲፈጽም ሚስቱ ብትጠይቀው ከማለበት ጊዜ ጀምሮ የአራት ወር ጊዜ ይጠብቃሉ። አርባ ቀኑ ሲሞላ ግንኙነት የመፈፀም ወይም በሚስቱ ጥያቄ መሰረት እንዲለያዩ ይገደዳል። በዚህ ወቅት ሴቲቱ የወሊድ ደም ካለባት ባልየው አይቆጠርለትም። (የወሊድ ደም ጊዜዋ ኢላእ እንዲጠቃለል ሆኖ አይቆጠርለትም።) ሚስቱ ከወሊድ ደም እስክትጠራ ያለው ጊዜ ለኢላእ ከሚያስፈልገው የወር አበባ ጋ አብሮ ወደ ኢላእ ጊዜ ይጨመራል። ይህ ከወር አበባ (ሐይድ) አንፃር በተቃራኒው ነው። የወር አበባዋ ከኢላእ ጊዜ ጋ ተጠቃልሎ ይቆጠርለታልና። በወር አበባ ያለፈው ጊዜ ለባልየው "ኢላእ" ውስጥ ይካተትለታል።
ሦስተኛ: ለአቅመ ህዋ መድረስ በወር አበባ እንጂ በድህረ ወሊድ ደም አይደለም። ምክንያቱም ሴት ልጅ ልታረግዝ የምትችለው መጀመርያውኑ የዘር ፈሳሽ የሚወጣት ሲሆን ነውና። ስለዚህም ለአቅመ ህዋ ደርሳለች የሚባለው በድህረ ወሊድ ደሟ ሳይሆን መጀመርያ የዘር ፈሳሽ በፈሰሳት ጊዜ ነው።
አራተኛ: የወር አበባ ደም ካቋረጠ በኃላ ወደ ልምዷ ቢመለስ በእርግጠኝነት የወር አበባ ነው። ለምሳሌ የወር አበባ ልምዷ ለስምንት ቀናት የሚዘልቅ ቢሆንና የወር አበባዋን ለአራት ቀናት ካየች በኋላ ለሁለት ቀናት አቋርጦ ከዚያም በሰባተኛውና በስምንተኛው ቀን ድጋሚ ቢመለስ ይህ የተመለሰው ደም በእርግጠኝነት የወር አበባ ነውና የወር አበባ ብይን ተፈፃሚ ይሆንበታል። ከወሊድ በኋላ በሚፈሰው ደም ግን ከአርባ ቀናት በፊት አቋርጦ በአርባ ቀናቱ ውስጥ ድጋሚ ከተመለሰ አጠራጣሪ ነውና ሶላቷንም የግዴታ ፆሚንም ጊዜውን ጠብቃ ታከናውናለች። ከግዴታ ተግባራት ውጪ ያሉት በወር አበባ ላይ ያለች ሴት የምትከለከለውንም ሁሉ በእርሷም ላይ እርም ይሆንባታል። የወር አበባ ላይ የነበረች ሴት ቀዷ (ማካካሻ) ማድረግ ያለባትን ሁሉ ይህችም ማካካስ አለባት። ይህ በሐንበሊይ የፊቅህ ዑለሞች ዘንድ የታወቀ ነው።
ትክክለኛው አቋም ደሙ የወሊድ ደም ሊሆን በሚችልበት ጊዜ ውስጥ ከሆነ የመጣው የወሊድ ደም ነው። ካልሆነ ግን የወር አበባ ነው፤ ካልቀጠለ በቀር (ከቆየ ግን) ኢስቲሓዷ ይሆናል።
ይህ አል-ሙግኒይ ላይ ከኢማሙ ማሊክ (ረሒመሁላህ) የተዘገበ ነው፦ ኢማሙ ማሊክ እንዲህ ብለዋል፦ "መፍሰሱ ከተቋረጠበት ቀን ከሁለት ወይም ከሦስት ቀናት በኋላ ደም ካየች የወሊድ ደም ነው፤ አለበለዚያ ግን የወር አበባ ነው።" ንግግራቸው አበቃ። የሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ (አላህ ይዘንላቸው) ምርጫም የሚያስፈርደው ይህንኑ ነው። በተጨባጩ እውነታ ስለ ደም ምንም ዓይነት አጠራጣሪ ነገር ሊኖር አይችልም። ነገር ግን ጥርጣሬው የሚመነጨው ሰዎች ካላቸው የእውቀትና የግንዛቤ ልዩነት አንጻር ነው። ቁርኣን እና ሐዲሥ በውስጣቸው የሁሉንም ነገር ማብራሪያ ይዘዋል። የበላይ የሆነው አምላክ አላህ ደግሞ ማንንም ሰው ሁለት ጊዜ እንዲጾም ግዴታ አላደረገበትም። ወይም ሁለት ጊዜ ጠዋፍ እንዲያደርግም አላዘዘም፤ እነዚህ ድርጊቶች ለመጀመሪያ ጊዜ ሲፈጸሙ የተበላሸ ነገር ካለ እና በትክክል ያልተሰሩ ሆነው ሲገኙ ተስተካክለው እንደገና መደገም አለባቸው ካልተባለ በቀር። ይሁን እንጂ አንድ ሰው አንድን ተግባር በችሎታው መጠን ከሰራ በኃላ ከማንኛውም ኃላፊነት ነፃ ነው። አላህ እንዳለው፦ "አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም።" [አል'በቀራ፡ 286] እንዲህም ብሏል፦ "አላህንም የቻላችሁትን የክል ፍሩት።" [አት'ተጋቡን፡ 228] በወር አበባ ደም እና በወሊድ ደም መካከል ካላቸው ልዩነት አምስተኛው: ከወር አበባ ልማዷ በፊት ንፁህ የሆነችን እንስት ባሏ ከእርሷ ጋ ግንኙነት መፈጸሙ የማይወገዝ የተፈቀደለት ነገር ነው። በወሊድ ደም ያለችን እንስት ግን ከአርባ ቀን በፊት ከነፃች ከሐንበሊ መዝሀብ በሚታወቀው መሰረት ባሏ ከእርሷ ጋ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረጋቸው የተወገዘ እንደሆነ ነው። ትክክለኛው አቋም ግን ከእርሷ ጋርግንኙነት ማድረግ የተወገዘ አለመሆኑ ነው። ይህም የአብዛኛዎቹ ዑለሞች ቃል ነው። ምክንያቱም "ከራህ" ማለትም "የተወገዘ" እንደሆነው ብይን መስጠት ሸሪዓዊ ብይን መስጠት በመሆኑ ሸሪዓዊ ማስረጃ የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ኢማሙ አሕመድ ከዑስማን ብን አቢ አል-ዓስ (ረዲየላሁ ዐንሁ) የዘገቡት (ሚስቱ) ከአርባ ቀን በፊት ወደርሳቸው ስትጠጋ "አትቅረቢኝ" ከማለታቸው በስተቀር ምንም ማስረጃ የለም። ይህ ደግሞ የተጠላ ነው ለማለት አያስችልም። ምናልባትም በንጽሕናዋ ላይ እርግጠኛ ካልሆነች ይህን ከመጠንቀቅ አኳያ ሊሆን የሚችል ነገር ነው። ወይም በግብረ ሥጋ ግንኙነት ምክንያት በውስጥ ያለውን ደም ማናጋት ሊኖር ይችላል በሚል ጥንቃቄ ለማድረግ ወይም ከዚህም ውጪ ላለ ምክንያት ሊሆን ይችላል። አላህ የበለጠውን ያውቃል!

*

# ክፍል ሰባት፡- የወር አበባን የሚከለክል ወይም የሚያመጣን ነገር ስለ መጠቀም እንዲሁም እርግዝናን ስለመከላከል እና ስለ ውርጃ

የወር አበባ መከላከያ ነገሮችን መጠቀም ሁለት ቅድመ መስፈርቶች ከተሟሉ የተፈቀደ ነው፦

አንደኛ:- እሷን ለመጉዳት የሚዳርግ መሆን የለበትም። በእርሷ ላይ ጉዳት ሊያመጣ እንደሚችል ስጋት ያለበት ከሆነ አይፈቀድም። አላህ እንዲህ ብሏልና፦ "በእጆቻችሁም (ነፍሶቻችሁን) ወደ ጥፋት አትጣሉ።" [አል'በቀራ፡ 195] "ነፍሶቻችሁንም አትግደሉ። አላህ ለእናንተ አዛኝ ነውና።" [አን'ኒሳእ፡ 29] ሁለተኛ፦ ከእርሱ ጋ የሚያያይዘው ጉዳይ ካለ የባሏ ፍቃድ ማግኘት። ይኸም ማለት ለምሣሌ፦ ዒዳዋን የምትቆጥር ሆና የእርሷን ወጪ የመሸፈን ግዴታ ባሏ ላይ ከሆነና የወር አበባን መከላከያ ተጠቅማ ጊዜውን ለማራዘም እና የእርሱን ወጪ ለመጨመር ልትጠቀመው ስለምትችል ነው። ስለዚህም የወር አበባን የሚከለክል ማንኛውንም ነገር ከእርሱ ፈቃድ ውጪ መጠቀም አይፈቀድላትም። በተመሳሳይም የወር አበባ መከላከያው እርግዝናን እንደሚከለክል የታወቀ ከሆነ የባል ፈቃድ ግዴታ ይሆናል። መፈቀዱ የተረጋገጠ ቢሆንም አስፈላጊ ካልሆነ በቀር አለመጠቁ የተሻለና በላጭ ነው። ምክንያቱም የተፈጥሮ ኡደትን እንዳለ መተው ለጤና እና ለደህንነት አስተማማኝ መንገድ ነውና።

የወር አበባ የሚያመጣን ነገር መጠቀምም እንዲሁ ሁለት ቅድመ መስፈርቶች ከተሟሉ ይፈቀዳል፦

አንደኛ፦ ግዴታ ተግባሮችን ለመተው ዘዴ አድርጋ መጠቀም የለባትም። ለምሣሌ ረመዷንን ላለመፆም የረመዷን ወር ሊገባ አካባቢ ብትጠቀመው ወይም ሶላትን ለመተውና ለመሳሰሉት ምክንያቶች ታስቦ መሆን የለበትም።

ሁለተኛ፦ የባሏ ፈቃድ መኖር አለበት። ምክንያቱም የወር አበባ መከሰቱ ከእርሷ ማግኘት የሚችለውን ሙሉ ደስታን እንዳያገኝ ያደርገዋልና ሙብቱን የሚከለክለውን ነገር ደግሞ ያለ እርሱ ፈቃድ መጠቀም አይፈቀድላትም። የተፈታች እንኳ ቢሆን ሚስቱን የመመለስ ሙብት ካለው ባልየው የመመለስ ሙብቱን (ጊዜው በማጠሩ ምክንያት) እንዲጣደፍ ያደርገዋልና።

እርግዝና የሚከላከሉ ነገሮችን መጠቀምን በተመለከተ ሁለት ዓይነት (ምልከታ) አለው፦

የመጀመሪያው፦ ሙሉ ለሙሉ በዘውታርነት የሚያቋርጠው ከሆነ ይህ አይፈቀድም። እርግዝና እንዲቋረጥ ስለሚያደርግ ዘር ይቀንሳል። የሙስሊሙን ማህበረሰብ ቁጥር መጨመር ከሚለው የሸሪዓ አላማ ጋር የሚጋጭም ይሆናል። የወለደቻቸው ልጆች ላለመሞታቸው ምንም አይነት ዋስትና የለምና ይህ ቢከሰት ልጅ አልባ መበለት ሆና ትቀራለች።

ሁለተኛው፦ የሚያቋርጠው ለተወሰነ ጊዜ ከሆነ። ለምሳሌ ሴቷ ብዙ ጊዜ የምትፀንስ ከሆነችና እርግዝናው ደግሞ የሚያደክማት ከሆነ። እርግዝናዋን በየሁለት ዓመቱ ወይም ተቀራራቢ በሆነ የግዜ ልዩነት አንድ ጊዜ ለመውለድ አቅዳ ከሆነ ይፈቀዳል። ይህም ሲሆን ግን ባሏ ከፈቀደ እና ምንም አይነት የጤና ጉዳት የማያመጣባት ከሆነ ነው። የዚህም ማስረጃው ሶሓቦች በነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ጊዜ ከሚስቶቻቸው ጋር ግንኙነት ሲፈፅሙ ሚስቶቻቸው እንዳይፀነሱ "ዓዝል" ያደርጉ ነበር ይህንንም አልከለከሏቸውም። "ዓዝል" ማለት ከሚስቱ ጋ ግንኙነት እየፈፀመ ልክ የዘር ፈሳሽ ሊወጣ ሲል ብልቱን ከሴቷ ብልት ውጭ በማድረግ የወንዴ ዘሩን ወደውጭ ማፍሰስ ነው።

ፅንስን የሚያጨናግፉ ነገሮችን መጠቀምን በተመለከተ ሁለት ዓይነት (ምልከታ) አለው፦

የመጀመሪያው፦ በእናቱ ማህፀን ውስጥ ያለውን ነገር ለማስወገድ ከሆነ። ፅንሱ ነፍስ ከተዘራበት በኋላ ከሆነ የተከለከለ ነው። ምንም ጥርጥር የለውም። ምክንያቱም የተከለከለች ነፍስን ያለ አግባብ ገድሏልና። የተከለከለን ነፍስ መግደል ደግሞ በቁርኣን፣ በሱና እና በሙስሊሞች ስምምነት የተከለከለ ነው። ነፍስ ከመዘራቱ በፊት ያለውን በተመለከተ ይፈቀዳል ወይስ አይፈቀድም በሚለው ላይ ሊቃውንት ተለያይተዋል። ከእነርሱ መካከል የፈቀደ አለ፤ ከመካከላቸውም የከለከለ አለ። ተከታዩን ያሉ አሉ፦ ዐለቃህ እስካልሆነ ማለትም አርባ ቀን እስካልሞላው ይፈቀዳል። ብለዋል። ሌሎቹ ደግሞ፦ የሰው ልጅ ቅርጽ እስካልያዘ ድረስ ይፈቀዳል ብለዋል።

ለጥንቃቄ ሲባል ፅንስ ማስወረድ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ለምሳሌ እናትየው ታምማ ፅንሱን መሸከም የማትችል ከሆነ ወይም የመሳሰሉትን ምክንያቶች ከሌሉ አለማድረጉ ነው። የሰው ልጅ ቁመና የሚላበስበት እና የተከለከለበት ጊዜ ካላላፈ በስተቀር ፅንሱን ማቋረጥ ይፈቀዳል። አላህ የበለጠውን ያውቃል።

ሁለተኛ ፦ በእናቱ ማህፀን ውስጥ ያለውን ፅንስ ለማስወገድ ለማስወገድ አስበው ካልሆነና የእርግዝና ማብቂያዋ ሲቀርብና መውለጃ ጊዜዋ ሲደርስ ለማስወረድ መሞከር ይህ ይፈቀዳል። ነገር ግን በእናቲቱ ወይም በልጁ ላይ ጉዳት የማያደርስ ከሆነ ነው። እንዲሁም የቀዶ ጥገና የማያስፈልገው ከሆነ ነው። የቀዶ ጥገና ሕክምና አስፈላጊ ከሆነ አራት ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ፦

የመጀመርያው፦ እናት እና ልጅ በህይወት የሚቆዩ ከሆነ፦ አንገብጋቢ ካልሆነ በስተቀር ቀዶ ጥገና ማድረግ አይፈቀድም። (ለምሳሌ) ለመውለድ አስቸጋሪ ሆኖባት ቀዶ ጥገና አስፈላጊ ከሆነ። ይህም የሆነበት (ያልተፈቀደበት) ምክንያት የሰውነት አካል ለሰው ልጅ የተሰጠን አደራ በመሆኑ ነው። ትልቅ ጥቅም ለሚያስገኝ ነገር ካልሆነ በስተቀር ጉዳት የሚያደርስበት ተግባር መፈፀም የለበትም። ቀዶ ጥገናው ምንምም ጉዳት አያደርስም ብለው አስበው ምናልባት ጉዳቱ ሊያስከትል ይችላል።

ሁለተኛ፦ ሁለቱም እናት እና ልጇ የሚሞቱ ከሆነ፤ ምንም ጥቅም ስለሌለው ቀዶ ጥገና ማድረግ አይፈቀድም።

ሦስተኛ፦ እናቲቱ በህይወት የምትቆይ እና ፅንሱ ደግሞ የሚሞት ከሆነ። በእናት ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ተብሎ ካልተፈራ የሞተውን ፅንስ በቀዶ ጥገና ማስወገድ ይፈቀዳል። አላህ የበለጠውን ያውቃል ፅንስ ከሞተ ያለ ቀዶ ጥገና መውጣት አይችልም። በሆዷ ውስጥ መቆየቱ ወደፊት ማርገዝ እንዳትችል ይከለክላታል። በጣም ከባድ ችግር ነው። ምናልባትም ይህ ሴትየዋን ከቀድሞ ባሏ ጋ በፍቺ ላይ ሆና ኢዳዋን እየቆጠረች (የጥበቃ ጊዜ ውስጥ) ከነበረች እንደ አይም (እመበለት) ያደርጋታል

አራተኛ፦ እናቲቱ ሞታ ፅንሱ በህይወት የሚቆይ ከሆነ፦ ፅንሱ በህይወት መትረፉ ተስፋ የሚደረግ ካልሆነ ቀዶ ጥገናውን ማከናወን አይፈቀድም።

በህይወት መትረፉ ተስፋ የሚደረግ ከሆነና የተወሰነው አካሉ ከእናቱ ሆድ ወጥቶ ከሆነ የቀረው ለማውጣት የእናትን ሆድ መቅደድ (መክፈት) ይቻላል። ምንም አካሉ ካልወጣ ደግሞ አንዳንድ የፊቅህ ሊቃውንት አላህ ይዘንላቸው ፦ ፅንሱን ለማውጣት የእናቱን ሆድ መክፈት (ቀዶ ጥገና ማድረግ) አካል እንደማጉደል ይቆጠራልና አይቻልም ብለዋል። ትክክለኛው አቋም የእናቲቱ ሆድ ሳይከፈት (ያለ ቀዶ ጥገና) ልጁን ማውጣት የማይቻል ከሆነ መክፈት ይፈቀዳል። ይህ የኢብኑ ሁበይራህም ምርጫ ነው። አል'ኢንሳፍ (በተሰኘው ድርሳናቸው) ላይ፦ ተመራጭ (በላጭ) ነው ብለዋል። በዚህ ላይ የኔ አስተያየት፦ በተለይ ባለንበት ዘመን ኦፕራሲዮኑ

(ቀዶ ጥገና) አካል ማጉደል ሊባል አይችልም (አይደለም)። ምክንያቱም ሆዱ ከተሰነጣጠቀ በኋላ መልሶ ይሰፋል። እንዲሁም በሕይወት ያለ ሰው ክብርና ከሞተ ሰው ክብር እጅግ የበለጠ ነው። ምንም የማያውቅን (ጥብቅ ህፃን) ከጥፋት ማዳን ግዴታ ስለሆነ። በማህፀን ውስጥ ያለው ጥብቅ የሆነ ሰው ነው። እርሱን ማዳን ግዴታ ነው። አላህ ይበልጡን ያውቃል።

ማሳሰቢያ፦ ቀደም ብለን በጠቀስናቸው ፅንስ ማቋረጥ በሚቻልባቸው ሁኔታዎች በጉዳዩ ላይ ሙብት ያለው አካል ለምሳሌ እንደ ባል ያለ ሰው ፈቃድ ሊሰጠው ይገባል።

በዚህ አስፈላጊ ርዕስ ላይ ለመጻፍ የፈለግነው ጉዳይ እዚህ ጋ አበቃ፤ በውስጡ ራሳችንን የጉዳዩን መሰረታዊ ነጥቦችና ደንቦች ላይ ብቻ ተገድበናል። አለበለዚያ በሴቶች ላይ የሚከሰቱ ነገሮችን ቅርንጫፎቹ እና ዝርዝር ነጥቦቹን ካነሳን ማለቂያ የሌለው ባህር ባህር ውስጥ መግባት ነው። ነገር ግን አስተዋይ ሰው ቅርንጫፋዊ ጉዳዮችን ወደ መሰረታቸው፤ ዝርዝር ጉዳዮችን ወደ ሁለንተናዊ እና መቆጣጠሪያዎቻቸው መመለስ ይችላል፤ ነገሮችን እንደየ አምሳያቸው ቂያስ ያደርጋል። ሙፍቲ (ፈትዋ የሚሰጥ) የሆነ ሰው በአላህና በፍጡራኑ መካከል መልእክተኞቹ ያመጡትን ለማድረስ ድልድይ መሆኑን ማወቅ ይገባዋል። ለፍጡራኑ ለማብራራት፤ በቁርኣን እና በሱናም ላይ ተጠያቂ ነው። አገልጋዩ የመረዳትና የመተግበር ኃላፊነት የተጣለበት ሁለቱ ምንጮች ናቸው። ከቁርኣን እና ሱና ጋ የሚጋጭ ነገር ሁሉ ስህተት ነው። ወደ ተናጋሪው ሰው ንግግሩን መመለስ ተገቢ ነው። በእርሱ መሥራት አይፈቀድም። የተናገረውም ሰው ምናልባት ሙጅተሂድ የሆነና ለስህተቱ ኡዝር የሚሰጠው እንደውም በኢጅቲሀዱ (እውነታ ላይ ለመድረስ ባደረገው ጥረት) ምንዳ የሚያገኝ ይሆናል፤ ነገር ግን ከእርሱ ውጪ ያሉ ሌሎች ሰዎች የእርሱን ስህተት መቀበል አይፈቀድላቸውም።

ሙፍቲ (ኒያውን) ልባዊ ሃሳቡን የበላይ ለሆነው አላህ ጥርት የማድረግ ግዴታ አለበት። በሚያጋጥመው ነገር ላይ ሁሉ የአላህን እገዛ ሊፈልግ ይገባል፤ ትክክለኛውን ጎዳና እንዲገጥመውና ጽናትንም እንዲሰጠው ሊለምን ይገባል።

በአላህ ኪታብ (ቁርኣን) እና በነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ሱና ውስጥ ያለውን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት፣ ጥናት ማድረግ እና መመርመር ግዴታ ይሆንበታል። እንዲሁም ሁለቱን ለመረዳት የሙስሊም ሊቃውንት የሰጡትን ማብራሪያ ማጥናት ያስፈልጋል።

ብዙ ጊዜ አንዳንድ ሁኔታዎች ይከሰቱና ስለ ሁኔታው የሊቃውንትን ንግግር የሚፈልግ ሰው ልቡን የሚያረካ ብያኔ አያገኝም ወይም ሰውዬው ደግሞ ስለ ጉዳዩ የሚያትት ምንም ነገር ላያገኝ ይችላል። (በዚህ ጊዜ) ሰውየው ወደ አላህ ኪታብ (ቁርኣን) እና ወደ ሱና ከተመለሰ። እንደ ኢኽላስሱ፣ ዕውቀቱ እና በግንዛቤው መጠን ወደ ግልፅ እና ቅርብ ማስረጃ መድረስ ይችላል።

ችግር (ግልፅ ያልሆነ ነገር) በሚገጥመው ጊዜ ሙፍቲው ብይን ለመስጠት የተረጋጋ መሆን አለበት፤ መጣደፍ የለበት። ስንትና ስንት ብይኖች ናቸው ተጣድፎ የወሰናቸው ከዚያም በጥሞና ከተመለከተ በኋላ እርሱ ስህተት እንደሆነ ግልጽ የሆነለትና ፀፀት ውስጥ የገባ። ምናልባትም ያመለጠውን ነገር መልሶ ማግኘት የማይችልበት ደረጃ ደርሶም ይሆናል።

ሰዎች የአንድን ሙፍቲ እርጋታውን ጉዳዮችን የማረጋገጥ አቅሙን ከተመለከቱ የሚናገረውን ንግግር አምነው ይቀበላሉ ቦታም ይሰጣሉ። ያለበለዚያ ግን ችኩል ሆኖ ከተመለከቱ፤ ፈትዋ ሲሰጥ ካጣደፈና ከቸኮለ በሚሰጣቸው ብይን ላይ እምነት ሊያጡ ስለሚችሉ ራሱንም ሆነ ሌሎችን እርሱ ዘንድ ካለው ዕውቀት እንዳይጠቀሙ ያደርጋቸዋል።

እኛንም ሆነ ሙስሊም ወንድሞቻችንን ወደ ቀጥተኛው መንገድ እንዲመራን፣ ሁሉን ቻይ የሆነውን አምላክ ጥበቃውን እንዲሰጠን እና ከክፋም እዲያድነን እንለምነዋለን። የአላህ ሰላት እና ሰላም በነብያችን ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸው እና በባልደረቦቻቸው ላይ ሁሉ ይስፈን። በጸጋው በጎ ሥራ ሁሉ የሚፈፀመው አላህ ምስጋና ተገባው!

ጸሐፊ የአላህን እዝነት ከጃይ የሆኑት<br>ሙሐመድ ቢን ሷሊሕ አል'ዑሠይሚን<br>ዕለተ ጁሙዓ ረፋዱ ላይ<br>ሸዕባን 14 1392 ሂጅራ<br>*

የሴቶችን ተፈጥሯዊ ደም የተመለከተ አጭር መልዕክት
ምዕራፍ አንድ፡ የወር አበባ ምንነት እና ሚስጥሩን በተመለከተ
ምዕራፍ ሁለት: የወር አበባ የሚጀምርበት እና የሚያቆምበትን የጊዜ ገደብ በተመለከተ
ክፍል ሦስት: የወር አበባ መዛባትን በተመለከተ
ክፍል አራት፦ የወር አበባን የተመለከቱ ሕግጋቶች
ክፍል አምስት፡ ኢስቲሓዷን የተመለከቱ ሕግጋት
ምዕራፍ ስድስት፦ ስለ ወሊድ ደም እና ሕግጋቶቹ
ክፍል ሰባት፦ የወር አበባን የሚከለክል ወይም የሚያመጣን ነገር ስለ መጠቀም እንዲሁም እርግዝናን ስለመከላከል እና ስለ ውርጃ